# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 017 መስከረም 17 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡- ኢዮብ ተፈራ

# "መስቀል በዓልን የምናከብረው ኃይለ እግዚአብሔርን ለማሰብና ቃለ ድህነቱን ለማሥረጽ ነው"

- ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- መስቀል በዓልን የምናከብረው ኃይለ እግዚአብሔርን ለማሰብ፣ በእርሱ ያለንን እምነት ለማስጠበቅና ቃለ ድህነቱን ለማሥረጽ ነው ሲሉ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ተናገሩ።

የመስቀል ደመራ በዓል በመስቀል አደባባይ በትናንትናው ዕለት በድምቀት ተከብሯል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፓትሪያሪክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያሪክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በዓሉን አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት፣ ወልደ እግዚአብሔር በሥጋ በዚህ ዓለም ተገለጦ በለበሰው ሥጋም በእኛ ፈንታ ቤዛ ሆኖ በመስቀል ላይ ሞተ ብለዋል።

የመስቀሉ ቃል ሰውን ለማዳን የተደረገ የእግዚብሔር ኃይል እንደሆነ አምነው ለሚቀበሉና ለሚኖሩበት የመጨረሻ

" መስቀል በዓልን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



"እኛ ኢትዮጵያውያን ከተደመርን እንደ ደመራው ብርቱ እንሆናለን፤ ከፍ ብለን እናበራለን"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- እኛ ኢትዮጵያውያን ከተደመርን እንደ ደመራው ብርቱ እንሆናለን፤ እንደ ደመራው ከፍ ብለን እናበራለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለ2017 ዓመት የመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለመስቀል በዓል በማህበራዊ የትስስር ገፃቸው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እንደገለጹት፤ መስቀል ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን በሁለት መንገድ የሚያሳይ በዓል ነው፡፡

ደመራው ከእንጨት ወደ ችቦ፤ ከችቦ ወደ ደመራ የሚያድግበት መንገድ መደመር ምን ያህል ኃይልና ጉልበት እንዳለው ያሳያል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ በሌላ በኩል ደግሞ መስቀል በተለያየ መንገድ፣ በተለያየ ባህልና አከባበር በብዙ ብሔረሰቦች መከበሩ በኅብረ ብሔራዊነታችን ውስጥ ያለውን ነባር ትሥሥር፣ የወል ትርክትና አንድነት የሚያሳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ እንዲህ ዓይነት በዓላት ሃይማኖታውያን ብቻ አይደሉም፡፡ የኅብረ ብሔራዊ አንድነት መገለጫዎች ጭምር ናቸው፡፡ በመደመር ውስጥ ያለውን ጥንካሬና ጉልበት የሚያሳዩ እና ትውልድ ለእኛ ትምህርት ያቆማቸው ምልክቶች ናቸው፡፡

ደመራውን በደመርን ጊዜ፤ ደመራውን

"እኛ ኢትዮጵያውያን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ሴሁን ካርታ



ግዩልዳን አምቢን



ፕራንክ ዊችባግ

# የመስቀል ደመራ ሳቢና አስደናቂ መሆኑን የውጪ ሀገራት ቱሪስቶች ገለጹ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የተከበረው የመስቀል ደመራ በዓል ሳቢና አስደናቂ መሆኑን በበዓሉ ላይ የተገኙ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ተናገሩ።

በመስቀል ደመራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ካናዳዊው ፕራንክ ዊችባግ፤ በዓሉ በሰዎች ብዛትና ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሲከበር መመልከቱ አግራሞት እንደፈጠረበት ገልጿል፡፡

"እኛ ኢትዮጵያውያን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





አቶ ሽመልስ አብዲሳ


ከንቲባ አዳነች አቤቤ


ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ (ዶ/ር)


ወይዘሮ አለሚቱ ኡሞድ


አቶ አሻድሊ ሀሰን

# የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች ለመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ

**- በዓሉን የሰላምና የአብሮነት ዕሴቶችን በማጠናከር ማክበር እንደሚገባ አመላክተዋል**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች ለመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ። በዓሉን የሠላምና የአብሮነት ዕሴቶችን በማጠናከር ማክበር እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልሰ አብዲሳ ለመስቀል በዓል ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ የደመራ እና መስቀል በዓል ያለንን ተጋርተን እርቅ በማውረድና ይቅርታ በማድረግ አንድነታችንን የምናጠናክርበት መሆን አለበት ብለዋል፡፡

በዓሉ ጎረቤት በአንድነት ሆኖ የሩቅና የቅርብ ወዳጅ ተሰብስቦ የሚያከብረው እንደሆነም ጠቅሰው፤ ሕዝቡ የደመራ እና የመስቀል በዓልን ሲያከብር ያለውን በመጋራት እርቅ በማውረድና ይቅርታ በማድረግ አንድነትን በማጠናከር መሆን አለበት ብለዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አረጋ ከበደ ለመስቀል በዓል ባሰተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ የመስቀል ደመራ በዓል በሃይማኖታዊም ሆነ በባህላዊ ትውፊቱ ትልቅ አስተምህሮት አለው። ከበረቱ፣ ከታገሉ እና ከጸኑ የማይሳካ ነገር እንደሌለ፤ የጸና የድል ባለቤት እንደሚሆን ከመስቀል ደመራ እንማራለን ብለዋል፡፡

እኛም በሚገጥሙን ፈተናዎች ሁሉ ሳንንበረከክ እንደ ደመራው በአንድነት ከቆምን አሁን ካሉብን ፈተናዎች ሁሉ አልፈን ከደመራው ብርሃን ማግስት የድካማችንን ውጤት ማየት እንደምንጀምር በማመን እንዲሁም የመስቀል ደመራ በዓልን ተሰባስበን ስናከብር ጠፍቶ የቆየውን አንድነት እና መሰባሰብን በማሰብ ብርሃኑ ጨለማውን እንደሚያጠፋው ሁሉ እኛም በፍቅር አንድ ሆነን እና ተሰባስበን ከሠራን ጠንካራ፣ የበለፀገች፣ ዘላቂ ሰላሟ እና አንድነቷ የፀና ኀብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያን ማየታችን አይቀርም ሲሉ ገልጸዋል።

አንድነታችን ፍፁም በሆነ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት ላይ በመገንባት እንደ ደመራችን ብርሃን ተስፋችንን እናድምቅ፤ በአንድነት ተሰባስበን የሚገጥሙንን ፈተናዎች በጽናት እንሻገር ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ዋጋ የተከፈለበት መስቀል ምሳሌነት በዚህች ምድር ስንኖር እርሰበርሳችን ያለ ምንም ልዩነት በፍቅር፣ በምህረት እና በመተሳሰብ እንድንኖር ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ መላው የከተማችን ነዋሪዎች የከተማችን ሌላኛው ድምቀት የሆነው የመስቀል ደመራ በዓል እንደ ምሳሌነቱ የሰው ልጆችን ሁሉ በመውድ፣ እርስበርስ በመተባበር፣ በመከባበርና በፍቅር የዓሉን እሴቶች በመጠበቅ ባማረና በደመቀ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የበኩላችሁን እንድትወጡ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በተመሳሳይ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር እንዳሻው ጣሰው ባስተላለፉት መልዕክት፤ የመስቀል በዓል የአብሮነትና የመተሳሰብ እሴቶች እንዲጠናከሩ በማገዝ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ነው ብለዋል፡፡

የመስቀል በዓል ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትውፊቶችን በማጠናከር የአብሮነትና የመተሳሰብ እሴቶች እንዲጠናከሩ በማገዝ የበኩሉን ሚና እያበረከተ እንደሚገኝ የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የመስቀል በዓል ሃይማኖታዊና ባህላዊ ገፅታ ያለው መሆኑን በማንሳት በዓሉ ተራርቀው የሠነበቱ ቤተሰቦች የሚገናኙበት፣ ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ትስስሮች የሚታደሱበት ነው ብለዋል።

የመስቀል በዓል ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትውፊቶችን በማጠናከር የአብሮነትና የመተሳሰብ እሴቶች እንዲጠናከሩ በማገዝ የበኩሉን ሚና እያበረከተ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የዘንድሮውን የመስቀል በዓል ስናከብር ለሠላምና ለአብሮነት መሠረት የሆኑ እሴቶችን በማጠናከር፣ ለጋራ ለውጥና ዕድገት በጋራ ለመትጋት ቃላችንን እያደስን መሆን ይኖርበታል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው፤ በዓሉ የአንድነት፣ የአብሮነት እና የመደመር፣ የኃያልነት የመድመቅ መሠረት መሆኑን ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን የቱንም ያህል ችግሮች፣ መከራዎች ቢፈትኑንም እነዚህን በጽናትና በትዕግስት በማለፍ እንደ ደመራው አንድ ሆነን ሀገራችን ከተስፋ ብርሃን ወደሚጨበጥ ብርሃን እያመራች ያለችውን መሰብሰባችን ታላቅ ሀገራዊ ብርሃንን እንድናበራ አይነተኛ ምሳሌያችን ነው ብለዋል።

ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰንም ለመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

በመልዕክታቸው፣ የመስቀል ደመራ በዓል ከኃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር ማህበራዊ ፋይዳው የጎላ ነው። በመሆኑም በዓሉን ስናከብር በአንድነት፣ በጋራና በመተሳሰብ ሊሆን ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በዓሉን በማክበር ሂደትም የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት፣ ድጋፍ ከሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ጎን መቆም ይገባል ያሉት አቶ አሻድሊ፣ በዓሉ በሠላም ተከብሮ እንዲጠናቀቅ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ አሳስበዋል፡፡

ርዕሰ መስተዳድር ጥላሁን ከበደ ለደመራና መስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፤ የመስቀል ደመራ በዓል፤ ከኢትዮጵያ አልፎ በመላው ዓለም የሰው ልጆች ቅርስነት የተመዘገበ፤ ሕዝቦችን ማስተሳሰር የቻለ ድንቅ ዕሴታችንና የሀገራችን ሀብት ነው ብለዋል፡፡

መስቀል የፍቅር፤ የአንድነትና የመተሳሰብ ተምሳሌት በመሆኑ፤ በዓሉን ስናከብር የመረዳዳትና የአብሮነት ዕሴታችንን በጠበቀ መልኩ በመጠያየቅ፤ በመተሳሰብ እና አብሮነታችንን በማጠናከር ሊሆን ይገባል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

ህዝበ ክርስትያኑ በዓሉን ሲያከብር ዕሴቱን ጠብቆ እንዲከበር በማድረግ የተቸገሩ ወገኖችን በማብላትና የተጠሙትን በማጠጣት ሊሆን ይገባል ያሉት ደግሞ የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ወይዘሮ አለሚቱ ኡሞድ ለመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ነው፡፡

ህብረተሰቡ የመተዛዘንና የመረዳዳት ባህሉን በመተግበር በዓሉን ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር እንዲያከብርም አሳስበዋል።

የተጀመረው የእድገትና የብልጽግና ጉዞ እውን እንዲሆን በየአካባቢያችን ሰላማችንን አጽንተን ያሉንን ጸጋዎች በመጠቀም ሙሉ አቅማችንን እና ትኩረታችንን በልማት ላይ ልናደርግ ይገባል ብለዋል።

# መድን ፈንድ በተያዘው ዓመት ሰባት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ዓረቦን ለመሰብሰብ አቅዷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ በ2017 ዓ.ም ሰባት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ዓረቦን ለመሰብሰብ ማቀዱን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ 2016 ዓ.ም የሥራ አፈጻጸምና የ2017 ዓ.ም የሥራ እቅድ አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ዋና ዳይሬክተር ደሳለኝ አምባው (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ፈንዱ በንግድ ባንኮችም ሆነ በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ ለሚቆጥበው ማህበረሰብ ዋስትና የሚሰጥ ሲሆን፤ በባንኮች ላይ ወይም ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ላይ የመውደቅ አደጋ ቢያጋጥም አስቀማጮች እስከ 100 ሺህ ብር ካሳ የሚያገኙበት ሥርዓት ዘርግቷል።


**ደሳለኝ አምባው (ዶ/ር)**

ፈንዱ አባል ከሆኑ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ካላቸው አማካይ ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ ዜሮ ነጥብ ሦስት በመቶ ዓረቦን የሚሰበስብ ሲሆን በዚህም ፈንዱ በ2016 ዓ.ም ስድስት ነጥብ 51 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን ገልጸዋል።

እንደ ዶ/ር ደሳለኝ ገለጻ፤ ተቋሙ በ2017 ዓ.ም ሰባት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ዓረቦን ለመሰብሰብና የተሰበሰበውን ዓረቦን በአግባቡ ኢንቨስት ለማድረግና ለማስተዳደር አቅዷል።

ከብር 100 ሺህ በላይ የተቀማጭ ገንዘብ ለአጣ ግለሰብ ወይም ድርጅት እስከ ብር 100 ሺህ ያለውን ገንዘብ ፈንዱ ተመላሽ የሚያደርግ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ የወደቀው ፋይናንስ ተቋም ሂሳብ አጣርቶ ተመላሽ ሊያደርግ እንደሚችል ገልጸዋል።

ዳይሬክተሩ እስካሁን ባለው ሁኔታ ወደ 97 በመቶ የሚሆኑ ገንዘብ አስቀማጮች በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ የያዙት ተቀማጭ ገንዘብ መጠን ከመቶ ሺህ ብር በታች በመሆኑ እነዚህ አስቀማጮች ከፈንዱ ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን የሚያገኙ መሆኑ ተናግረዋል።

ዶ/ር ደሳለኝ እንዳሉት፤ አንድ የፋይናንስ ተቋም ቢወድቅ ተቋሙን በመተካት ለገንዘብ አስቀማጮች ገንዘባቸውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከ90 ቀናት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ክፍያ ይፈጽማል።

ለዚህም አንድ የፋይናንስ ተቋም ቢወድቅ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈንዱን በመወከል ለገንዘብ አስቀማጮች ገንዘባቸውን የሚመልስበት አሠራር ለመፍጠር የመግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

ፈንዱ በአሁኑ ሰዓት 31 ባንኮችን እና 55 የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን በአባልነት ይዟል።



## "መስቀሉ ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ መተሳሰብና መከባበር እንዲሰፍን መልዕክት የተላለፈበት ነው"

**- ዳንኤል ሰይፈሚካኤል የሥነመለኮት መምህር**

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- መስቀሉ በሰው ልጆች መካከል ሁልጊዜም ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ መተሳሰብ እና መከባበር እንዲሰፍን መልእክት የተላለፈበት መሆኑን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጉባዔ አባልና የቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ገለጹ፡፡

መምህር ዳንኤል የመስቀል በዓልን በማስመልከት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመስቀሉ መልእክት ሁልጊዜም ሰላም ፍቅር፣ አንድነት፣ መተሳሰብ፣ መከባበር የተላለፈበት ነው፡፡ ስለሆነ ብሎ በማሰብ የሚያጋጩንን ነገሮች በማረም፣ ለሰላም፣ ለፍቅር፣ ለአንድነት እና ለመተሳሰብ ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል፡፡

‹‹መንፈሳዊ እና ማሕበራዊ ልእልና ባለባቸው መንገዶች በመመካከር፣ በመወያየት፣ በመግባባት፣ የሚለያዩ ነገሮችን በመተው የሚያግባቡንን ማጥበቅ ይገባናል›› ብለዋል፡፡

መለያየትና መጋጨት ምንም ትርፍ የለውም፤ ሰላም እና ፍቅርንም አይወልድም፤ ከጠብ የሚገኘው ጥፋት፣ የንብረት፣ የሕይወት የአካልና የብዙ ነገሮች ማጣትን ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የመስቀል ደመራ የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ በዓል መሆኑን በመጠቆምም፤ በተግባር የተገኘውን እርቅና ሰላም የምናከብርበት ፍቅርንም የምንገልጽበት እርቅን፣ ሰላምን፣ አንድነት እና ትስስር ሰብስቦ የያዘ ነው ብለዋል፡፡

የሃይማኖታዊ በዓልነቱ መሠረትም የጌታችን የመድኃኒታችን የእየሱስ ክርስቶስ መስቀል ለረጅም ጊዜ ከተቀበረበት ቦታ መገኘቱና መውጣቱን ምክንያት በማድረግ የሚከበር መሆኑንም አንስተዋል፡፡

መስቀሉን ስናከብር የሰውን ልጅ የሚከፋፍሉ ነገሮች እንዳይኖሩ ማድረጉን በማሰብ ሊሆን ይገባል ብለውም፤ በዓሉ የእርቅ፣ የሰላም እና የአንድነት እና የትስስር በዓል መሆኑን ነው የገለጹት፡፡

ቤተክርስቲያን የሰው ልጆች በማህበራዊ ትስስራቸው እርስ በእርስ እንዲዋደዱ ታስተምራለች፡፡ የሚፈጠሩ ማንኛውም አይነት ችግሮችና ልዩነቶች በቅራኔ በብጥብጥና በተለያዩ መንገዶች ሳይሆን እርስ በእርስ በመከባበር እና በመተሳሰብ ሊፈታ እንደሚገባም ታምናለች፡፡ ለትወልድ ቀሪ የሆኑ ጠባሳ ታሪኮችን መተው የለብንም ብለዋል፡፡

ከመስቀሉም የምንማረውና ክርስቶስ ወደዚህች ምድር የመጣው በሰው ልጅ ያለውን ጠብና ክርክር፣ ጥላቻ እና መለያየት ያጠፋ ዘንድ ነው፡፡ በዓሉን መልካምን በማሰብ ማክበር እንደሚገባም አመልክተዋል፡፡

መልካም ስናደርግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ፣ መልካም ገጽታው፣ ውበቱ ይመጣል፡፡ መስቀል በአደባይ የሚከበር ሁሉም ሰው አንድ ሆኖ አይደለም፡፡ በጣም ብዙ አይነት ነን፡፡ ነገር ግን አልተለያየንም መብዛት ውበት ነው፡፡

በዓሉ ደማቅ ሆኖ መከበሩ ማህበረሰብን ያገናኛል፣ የመስቀሉን ታሪክ እና ከነገረ መስቀሉ ጋር መሠረታዊ ትምህርቶች ለማስተላለፍ የሚጠቅም አሳታፊ የአደባባይ በዓል ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

መስቀል የሰው ልጅ ሃጢያቱ የተሻረበት፣ የሰውን ልጅ የዘላለም ሕይወቱን ያቋረጡ ነገሮች ሁሉ የተሸነፉበት እና ከባርነት ወደ ነጻነት፣ ከሞት ወደ ዘላለማዊ ሕይወት፣ ጠብና ግጭት ከነበረባቸው ተጻራሪ ነገሮች ተላቅቆ የፍቅር፣ የሰላም፣ የአንድነት የመተሳሰብ ምልክት የሆነበት ነው፡፡

ነገረ መስቀል በቤተክርስቲያን የሰው ልጅ የድህነት ታሪክ የሚነገርበት፣ የሰው ልጅ ፍጹም ድህነትንና ሰማያዊ ርስትን ያገኘበትን የምንተርክበት በዓል ነውም ነው ያሉት፡፡



# የኢሬቻ በዓል የገዳ ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ ለማክበር ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል

**- የዘንድሮው ኢሬቻ መስከረም 25 እና 26 ይከበራል**

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- የ2017 ዓ.ም ኢሬቻ በዓል የገዳ ሥርዓትና ዕሴትን በጠበቀ መልኩ ለማክበር ቅድመ ዝግጅት መደረጉን የአባገዳዎች ሕብረት አስታወቀ፡፡

የኦሮሞ አባ ገዳዎች ኅብረት የኢሬቻ በዓል አከባበርን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በዓሉ የገዳ ሥርዓትና ዕሴትን በጠበቀ መልኩ ለማክበር ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፡፡

የአባ ገዳዎች ኅብረት ሰብሳቢና የመጫ ኦሮሞ አባገዳ ወርቅነህ ተሬሳ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል አንድነትንና ሕብረትን በሚያጠናክር እንዲሁም የገዳ ሥርዓት እሴትን በጠበቀ መልኩ ለማክበር ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

እንደ አባገዳ ወርቅነህ ተሬሳ ገለጻ፤ በዓሉ መስከረም 25 ቀን በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፣ መስከረም 26 ቀን ደግሞ በቢሾፍቱ ሆራ ሃርሰዴ ይከበራል።

የኦሮሞ ሕዝብ ከሚያከብራቸው የእርቅና የሰላም ክብረ በዓላት መካከል ኢሬቻ አንዱ ነው።

ኢሬቻ የይቅርታና የአብሮነት በዓል በመሆኑ ሰላማዊነቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር በትብብር መሥራት እንደሚገባ የገለጹት አባ ገዳ ወርቅነህ፤ የበዓሉ ታዳሚያን የእርቅ፣ የፍቅርና የአንድነት ተምሳሌት በመሆን በዓሉን ሊያከብሩ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የኢሬቻ በዓል የሰላም በዓል በመሆኑ የኦሮሞን ባህልና ሥርዓት በተከተለ መልኩ መከበር እንዳለበት ገልጸው፤ በዓሉ ባህልና እሴትን ተከትሎ እንዲከበር ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የኦሮሞ ቱለማ አባ ገዳና የህብረቱ ምክትል ሰብሳቢ አባ ገዳ ጎበና ሆላ በበኩላቸው፤ በዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ላይ የሚታደም ማንኛውም አካል በይቅርታና በፍቅር መሆን አለበት ብለዋል፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ በገዳ ሥርዓት መተዳደር ከጀመረ ረጅም ጊዜ አስቆጥሯል ያሉት አባገዳ ጎበና፤ የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል በሆረ ፊንፊኔና ሆራ ሀርሰዴ በድምቀት ይከበራል ብለዋል።

የኦሮሞ ቄሮዎች፣ ቀሬዎችና ፎሌዎች የበዓሉ ባለቤት መሆናቸውን በመግለጽ፤ ኢሬቻ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ማስቻል እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ኢሬቻ የይቅርታ፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተለያዩ የሚገናኙበትና ፈጣሪ የሚመሰገንበት በዓል መሆኑን ተናግረዋል።

የአፈንቀሎ አባ ገዳና የህብረቱ ጸሃፊ አባ ገዳ አብዱረዛቅ መሐመድ በበኩላቸው፤ ኢሬቻ እርቅና ሰላም በመሆኑ የዘንድሮው ኢሬቻ በደስታ፣ በአንድነትና በፍቅር ሊከበር ይገባል ብለዋል።

በዓሉ ያለምንም እንከን እንዲከበር ሁሉም በጋራ መቆም እንዳለበት ገልጸው፤ በተለይም ወጣቱ ሚናውን በአግባቡ መወጣት እንዳለበት አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም በዓሉን ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር በመሆን እንዲያከብሩ ጥሪ አቅርበዋል።

በዓሉን ለመታደም የሚገኙ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የባህል ልብሳቸውን በመልበስ፣ በፍቅር፣ በአንድነትና በሰላም ማክበር እንደሚገባም ገልጸው፤ የኦሮሞ ቄሮዎች፣ ቀሬዎችና ፎሌዎች ኢሬቻ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር የበኩላቸውን እንዲወጡም ሕብረቱ ጥሪ አቅርበዋል።

# ኦሮሚያ ክልል በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ነጥብ ላስመዘገቡ ተማሪዎች ሽልማትና ማበረታቻ ሰጠ

ማርቆስ በላይ

አዳማ፡- የኦሮሚያ ክልል በ2016 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ነጥብ ላስመዘገቡ ተማሪዎች ሽልማትና ማበረታቻ ሰጠ፡፡

የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ከፍተኛ ነጥብ ያመጡ ተማሪዎች እና አስተዋፅኦ ላበረከቱ ባለድርሻ አካላት ያዘጋጀው የሽልማት መርሃግብር ትናንት ተካሂዷል።

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የማህበራዊ ዘርፍ አስተባባሪ አቶ ሳዳት በሻር በወቅቱ በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ ትምህርት ቤቶችን ከማስፋፋት ባሻገር ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ መሥራት ያስፈልጋል።

በክልሉ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋትና ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ በአዳሪና በልዩ ትምህርት ቤቶች የተገኙ ውጤቶችን ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ማሸጋገር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ትምህርት ላይ መሥራት ካልተቻለ ተወዳዳሪ ትውልድና የበለጸገ ሀገር መገንባት አይቻልም ያሉት አቶ ሳዳት፤ የመምህራን አቅምንና ተነሳሽነትን በማሻሻል ተማሪዎችን ውጤታማ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ በበኩላቸው፤ በክልሉ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከተፈተኑ መካከል 305 ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል።

በኦሮሚያ ስምንት ሺህ 520 ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባ ነጥብ አምጥተዋል ያሉት ኃላፊው፤ አዳሪ



ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ 13 ትምህርት ቤቶች ያስፈተኑትን ተማሪዎች በሙሉ አሳልፈዋል ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት ያስጀመራቸው የልዩና አዳሪ ትምህርት ቤቶች ውጤት እያስገኙ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን ጠቅሰው፤ ተማሪዎች ለትምህርት አለመዘጋጀት፣ የመምህራን አቅም ማነስና ተነሳሽነት፣ የትምህርት ቤቶች ግብዓት እጥረትና የአመራሮችና ባለድርሻ አካላት የዘርፉ ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓሉን ስናከብር ለሃይማኖታዊ እሴቶቹ ትኩረት በመስጠት ሊሆን ይገባል!

እንደ ሀገር የምናከብራቸው ሃይማኖታዊ/መንፈሳዊ በዓላቶቻችን በአብዛኛው ሰላም፣ ፍቅር፣ ተስፋ እና አብሮነትን የሚሰብኩ ናቸው። እነዚህ እሴቶች የሰው ልጅን የእለት ተእለት ሕይወት ትርጉም ያለው በማድረግ ፤ ፍጥረታዊ ማንነቱ ከደመነፍሳዊነት የላቀ መሆኑን በተጨባጭ የሚያመላክቱ ናቸው።

በተለይም ፍቅር አልባነት ፣ ከዚህ የሚመነጭ የሰላም እጦት እና ተስፋ ቢስነት ዓለምን በብዙ መልኩ እየተፈታተነ ባለንበት በዚህ ዘመን ፣ እነዚህን ሃይማኖታዊ /መንፈሳዊ በዓላት እንደ አንድ ትልቅ ሕዝብ ስናከብር፣ በዓላቱን ከሚያደምቁ የአከባበር ክንውኖች ይልቅ ፣ ለያዟቸው መንፈሳዊ እና ሠብዓዊ እሴቶች ትኩረት ልንሰጥ ይገባል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ ከሕዝባችን ከ80 ከመቶ የሚበልጠው ሃይማኖተኛ ነው። በአንድም ይሁን በሌላ ለፈጠረው አምላክ ከበሬታ ያለው ፣ ላስቀመጣቸው ሕጎች እና የአኗኗር ሥርዓቶች ተገዥ ለመሆን በተረዳው መጠን የሚንቀሳቀስ ፣ ለዚህ የሚሆን የተሰጠ ልብ እና አዕምሮ ባለቤት የሆነ ሕዝብ ነው።

ከሃይማኖታዊ/መንፈሳዊ እሴቶቹ የሚመነጩት ባህላዊ እሴቶቹም ቢሆኑ ፤ እነዚህኑ መንፈሳዊ እሴቶችን የሚያጎለብቱ ፣ በዕለት ተዕለት ሕይወቱ መመሪያ አድርጓቸው እንዲጓዝ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥሩ ናቸው። በብዙ መልኩ ፍቅር እና ሰላምን ፤ ተስፋ እና አብሮነትን የሚሰብኩ ፤ ለተግባራዊነቱም የተገራ ሥብዕና መፍጠር የሚያስችሉ ናቸው።

በዓላቱ ማህበረሰባዊ ተደርገው ሲወሰዱም ፤ በጊዜ ሂደት ትውልዶች በዓላቱ በያዟቸው ሃይማኖታዊ /መንፈሳዊ እሴቶች እየተገሩ ፤ ራሳቸውን ለእሴቶቹ ተገዥ በማድረግ ዘመን ተሻጋሪ ማኅረሰባዊ ማንነታቸውን አስቀጥለው መሄድ እንዲችሉ ፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት በትውልድ መካከል ለመፍጠር ነው።

እኛም የዛሬውን የመስቀል በዓልም ሆነ ሌሎች ሃይማኖታዊ/መንፈሳዊ በዓላትን እንደ ሀገር ስናከብር ፤ ዋነኛ ዓላማችን ፤ ከበዓላቱ ጋር የተያያዙ አስተምህሮዎችን ለማስታወስ እና ለአስተምህሮዎቹ ያለንን ታማኝነት ለማሳወቅ፤ የዕለት ተዕለት ሕይወታችን መርህ አድርገን ለመቀጠል ያለንን ቁርጠኝነት ለመግለጽ ጭምር ነው።

የመስቀል ጉዳይ የፍቅር እና ከፍቅር የሚመነጭ የእርቅ ጉዳይ ነው። ለፍቅር እና ለእርቅ የተከፈለን ዋጋ መዘከር ነው። ጠብ እና የጠብ ግርግዳ ስለፈረሰበት የመስቀል ሥራ ማሰብ እና ማሰላሰልን ፤ ለዚህ ለሚሆን መንፈሳዊ መታደስ ራስን እንደ አንድ ትልቅ ሃይማኖተኛ ማኅበረሰብ ማዘጋጀት የሚጠይቅ ነው።

ይህ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን ካለንበት አሁናዊ ፈተናዎች ለዘለቄታ ለመውጣት ያለን የመውጫ ብቸኛው መንገድ ነው። ወደ ቀደመው ፍቅራችን በመመለስ ራሳችንን ለእርቅ ማዘጋጀት ፤ በእርቅ ሰላማችንን እና አብሮነታችንን በጠንካራ መሠረት ላይ ማዋቀር ይኖርብናል።

ይቅር ባይነት የመስቀሉ ትልቁ ሥራ እንደመሆኑ መጠን የመስቀልን በዓል ስናከብር ፤ በይቅር ባይነት መንፈስ ልንታደስ ፤ የጣልነውን ይቅር የመባባል መንፈሳዊ እሴት ከጣልንበት አንስተን ፤ ይቅር በተባልንበት መጠን ይቅር ልንል፤ በዚህም ሀገራዊ ሰላም እና አብሮነታችንን ልንጠብቅ ይገባል።

ከመራራነት እና መራራነት ከሚፈጥረው ጥላቻ እና የልብ ድንዳኔ ወጥተን ፤ ከልጅነት እስከ አዋቂነት ፤ ከአዋቂነት እስከ እርጅና ዘመናችን ከኛ ባልተለዩን ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን ራሳችንን እና የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ልንመረምር ፤ በብዙ የራቅናቸውን ያህል ልንቀርባቸው እና የሕይወታችን መርህ ልናደርጋቸው ይገባል።

የመስቀል በዓል መከበር ዋንኛ ዓላማም ፤ በበዓሉ ሃይማኖታዊ እሴቶች ራሳችን በአግባቡ እንድንመረምር፤ በመረመርነው መጠን ለራሳችን ታማኝ ሆነን ከራሳችን ጋር እርቅ እንድናደርግ ነው፤ ይህ ደግሞ በዓሉ የእኔ ነው ከሚል ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ የሚጠበቅ ትልቅ የቤት ሥራ ነው!


አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መስቀል አበባ ውብ አበባ…

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የመስቀል በዓል በወርኃ መስከረም አጋማሽ የሚከበር ሲሆን በዚህ ወቅት በተለይም በገጠሩ የሀገራችን ክፍል አንዳንድ የሰብል ዓይነቶች ማሸት የሚጀምሩበት እና የበቆሎ እሸት የሚደርሱበት ፤ የጎመን ድስት ወጥቶ የገንፎ ድስት የሚጣድበት ፤ አደይ አበባ የሚፈካበት ነው። አርሶ አደሩም በባለፈው ዓመት የመርኸር እርሻ ከዘራው ምርት መቅመስ የሚጀምርበት ፤ ጎተራው ተሟጦ የነበረው አርሶ አደር ጎተራውን ከጓሮው የሚያደርግበት፤ ልጅ ከብቱ የሚጠግብበት የሽግግር ጊዜ በመሆኑ ልዩ ስሜትን ይሰጣል። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ንብ አናቢዎችም ማር መቁረጥ የሚጀምሩበት መስከረም 17 ነው። በዚህ ቀን የተቆረጠን ማር እንደመድሃኒት ይቆጥሩታል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አማኞች ዘንድ የአሌክሳንድሪያው ፓትርያርክ በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ገዢ ለነበሩት ዐፄ ዳዊት ክርስቶስ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀል ስላበረከቱላቸው ግማደ መስቀሉ በሀገራችን ኢትዮጵያ ይገኛል የሚል እምነት አላቸው። በመሆኑም የዓሉ አከባበር በኢትዮጵያ ልዩ ድባብ ያለው ነው።

እንደሊቃውንት ገለጻ፤ መስከረም 17 ቀን የሚከበረው የመስቀል በዓል ለሦስት መቶ ዓመታት ተቀብሮ እና ቆሻሻ ሲጣልበት የቆየውን ክርስቶስ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀል ለመፈለግ ንግሥት እሌኒ ቁፋሮ ያስጀመረችበት ቀን ነው። መስቀሉን ለመፈለግ መስከረም 17 ቀን ቁፋሮው ይጀመር እንጂ የተገኘው መጋቢት 10 ቀን ነው። ነገር ግን መጋቢት 10 ቀን በየዓመቱ ጾመ ኢየሱስ ላይ የሚውል በመሆኑ መስቀሉ ለማውጣት ቁፋሮ በተጀመረበት መስከረም 17 ቀን እንዲከበር ተደርጓል፡፡

ደመራ የሚደመረውና የሚለኮሰው መስቀሉን በመፈለግ ሂደት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን ለማመላከት ነው። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔም በድህረ ገፁ ባወጣው አንድ መረጃ ኢትዮጵያውን የሚያከብሩት የመስቀል በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ትክክለኛው መስቀል ተቆፍሮ የተገኘበትን ቀን ለመዘከር እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ደመራ የሚደመረውና የሚለኮሰው መስቀሉን በመፈለግ ሂደት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን ለማመላከት ነው

የበዓሉ አከባበር እንደየቦታው ወግ ፣ ባህል፣ ዕሴት፣ ትውፊት በተወሰነ ደረጃ ይለያያል። በአንዳንድ አካባቢዎች የመስቀል ደመራ በዋዜማው እንዲበራ ሲደረግ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ በመስቀል ቀን ጠዋት ደመራ ተደምሮ እንዲበራ ይደረጋል። በመስቀል ደመራ ላይ አደይ አበባና ለምለም ቄጠማ ጣል ጣል ማድረግ የተለመደ ነው። በሕዝቡ ዘንድም መስቀልን ከአደይ አበባ ጋር የማያያዝ ነገርም ይታያል። በቤተክርስቲያን ዝማሬም

« **መስቀል አበባ ነህ ውብ አበባ**
**አደይ አበባ ነሽ አበባ**
**መስቀል አበባ ተቀብሮ ሲኖር**
**አደይ አበባ ሥነ ስቅለቱ**
**መስቀል አበባ እሌኒ አገኘች**
**አደይ አበባ ደገኛይቱ …**
መስቀል አበባ ወንዙ ጅረቱ አደይ አበባ ሸለቆው ዱሩ
መስቀል አበባ አሸብርቀው ደምቀው አደይ አበባ ላንተ መሰከሩ። ...» እያሉ ይዘምራሉ፡፡

ከአስር ዓመት በፊት በመስቀል አደባባይ ደመራ ወጣቶቹ ሲዘምሩ በብዛት በወረቀት የተሠራ አደይ አበባ ይዘው በዝማሬና በዝማሜ ስለነበር፤ ዛሬ በየቦታው ለምናየው ለሴቶች የጆሮና የፀጉር ጌጥ ፣ ለአልባሳት፣ ለመኖሪያ ቤቶች መስኮትና የግድግዳ ጌጥ እንዲሆኑ አዎንታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል። ዛሬ እንደ ጌጥ የሚያገለግለው አሪቲፊሻሉና ትልልቁ አደይ አበባ ገበያው በመስከረም ሲብት እንዲህ ሊደራና በሰዉ ዘንድ ሊወደድ የቻለው በሰንበት ተማሪዎች በመስቀል ዝማሬ በፈጠሩት ኩነት ነው።

መስቀል ለአንድንድ ብሔረሰቦችም እንደመታወቂያ ምልክትም ነው። ለምሳሌ መስቀል በጉራጌ ብሔረሰብ የተለየ ድባብ ያለው ነው። የጉራጌ ብሔረሰብ ዓመቱን ሙሉ በአዲስ አበባ እና ሌሎች ትልልቅ ከተሞች ከላይ ታች ወጥቶና ወርዶ፤ ነግዶ ሠርቶ ያገኛትን ገንዘብ ቋጥሮ ወደ ቤተሰቦቹ ቀየ ገጠር ድረስ ሄዶ እርድ አርዶ፣ ቆጮውን ፣ የጎመን ክትፎውንና የስጋውን ክትፎውን አዘጋጅቶ የሚያከብረው በዓል ነው።

መስቀል የሚከበረው መስከረም ጠባ አዲስ ዓመት ገባ በሚል ድባብ ስለሆነ ፤ ዓመቱን ሙሉ ሠርቶ የደከመ መንፈሱን ያድስበታል። የተለያዩ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክንዋኔዎችን ይፈጽምበታል። በመስቀል በዓል ተያይተው የተዋደዱ ለአቅመ አዳም እና ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ወጣቶችም ሦስት ጉልቻቸውን ይመሠርቱበታል። አጋጣሚውን «በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ» አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡

በዓሉ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ፓትርያርክን ጨምሮ ጳጳሳት ፣ ቀሳውስት ሌሎች የሃይማኖት አባቶች ፣ ዲፕሎማች እና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንዲሁም ቱሪስቶችና የከተማው ነዋሪዎች የሚታደሙበት ነው። በዓሉ ሃይማኖታዊ ይሁን እንጂ ባህላዊ ዐውድና ድባብ ያለው ነው። በዓሉ በአደባባይ በተለያዩ መንፈሳዊ ዝማሪዎች እና ትእይንቶች ደመራ በማብራት በልዩ ድምቀት የሚከበር ነው። ቄሳውስት እና ዲያቆናት እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ቤት ዘማርያን ለአእምሮ ደስታን የሚፈጥሩ የያሬድ ዝማሬዎች የሚያቀርቡትን ነው።

« **መስቀል ብርሃን ለኩሉ ዓለም**
**መሠረተ ቤተክርስቲያን**
**ወሃቤ ሰላም መድሃኒዓለም**
**መስቀል ኃይልነ ለእለ ነአምን**» እያሉም ይዘምራሉ። ትርጓሜውም
መስቀል ብርሃን ነው ለመላው ዓለም
መሠረት ነው ለቤተክርስቲያን
ሰላምን ሰጪ ነው መድሃኒዓለም
መስቀል ኃይል ነው ለእኛ ለምናምነው፡፡» ማለት ነው።

በነገራችን ላይ መስቀል በሚከበርበት መስከረም 17 ቀን በየዓመቱ የዓለም የቱሪዝም ቀንም ታስቦ ይውላል። ይህ ደግሞ በዩኔስኮ የተመዘገበውን የመስቀል በዓል በቱሪስቶች ዘንድ ልዩ ቦታ እንዲሰጠው እድል ይፈጥራል። ሀገራችን ከቱሪዝም የምታገኘውን ገቢ ከፍ ለማድረግ ያግዛል፤ ለብዙ ወጣቶችም የሥራ እድል ፈጥራል። ስለሆነም አጋጣሚውን ለመጠቀም እኛ ኢትዮጵያውያን ከመነቃቀፍ ወጥተን በመተቃቀፍ ከቱሪዝሙ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ እጅ ልእጅ እንያያዝ! መልዕክቴ ነው።

# የመስቀል ደመራ በዓል ሰዎችን የሚያቀራርብ የፍቅር፣ የሰላምና የአንድነት ተምሳሌት መሆኑ ተገለጸ

## - የመስቀል ደመራ በዓል በድምቀት ተከብሯል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የመስቀል ደመራ በዓል ሰዎችን የሚያቀራርብ የፍቅር፣ የሰላምና የአንድነት ተምሳሌት መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

የ2017 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ በተለያዩ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች በትናንትናው ዕለት በድምቀት ተከብሯል።

የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ሸዊት ሻንካ በበዓሉ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተቀብሮ የነበረው መስቀል የወጣበትን ቀን በውብ ኃይማኖታዊ ሥርዓት በማክበር የመስቀሉን መገኘትና ተቀብሮ አለመቅረትን በማብሰር ግማደ መስቀሉን ይዛና ጠብቃ በማኖሯ እንኮራባታለን ብለዋል።

ኢትዮጵያ በበርካታ መዛግብታዊ ማስረጃ ከዓለም ቀዳሚ እና የገዘፈ የታሪክ ባለቤት ሀገር ናት መሆኗን ገልጸው፤ ለዚህ ማሳያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሚገኙ ዕንቁ እሴቶች መካከል የመስቀል ደመራ በዓል አንዱ መሆኑን ተናግረዋል።

በሁሉም አካባቢዎች በድምቀት የሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል ባህላዊ ትዕይንትና ሕብረብሔራዊ አንድነትና አብሮነት ጎልተው የሚታዩበት የጋራ በዓል መሆኑን አስታውቀዋል።

መስቀል የአብሮነት የአንድነት፣ የሰላምና የፍቅር ምልክት በመሆኑ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ በሙሉ ልብ መነሳሳትና



ሸዊት ሻንካ



ሒሩት ካሳው (ዶ/ር)

ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ብርቅየና ባህላዊ እሴቶች እንዲለሙ፣ እንዲጠበቁና ለትውልድ እንዲሻገሩ ለማስቻል ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቁርጠኝነት እንደሚሠራ አረጋግጠዋል።

መስቀል የአብሮነትና የፍቅር ምልክት በመሆኑ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባም ሚኒስትሯ ገልፀዋል።

በዚሁ መርሐግብር የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በተወካያቸው በአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) በኩል መልእክት አስተላልፈዋል።

በመልዕክታቸውም የመስቀል ደመራ በዓል ከኃይማኖታዊ እሴቱም ባለፈ የሀገራችን በጎ ገጽታ ማሳያና የቱሪዝም ገቢን የሚያሳድግ በመሆኑን ኃይማኖታዊ እሴቱን ጠብቆ ለትውልድ ማሻገር ይገባል ብለዋል።

የመስቀል ደመራ በዓል ሰዎችን የሚያቀራርብ የፍቅር፣ የሰላምና የአንድነት ተምሳሌት በመሆኑ ሁላችንም ልንጠብቀው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በትውልድ ቅብብሎሽ ረጅም ዘመናትን ተሻግረው ላለንበት ዘመን የደረሱ በርካታ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች ባለቤት ናት ያሉት ከንቲባዋ፤ እነዚህ ብርቅዬ እሴቶቿ ለሕዝቦቿ ኩራት ከመሆን አልፈው ለዓለም ሕዝብ ሀብት የሆኑ ናቸው። ከእነዚህም መካከል የመስቀል ደመራ በዓል ነው ብለዋል።

ይህ የፍቅርና የሰላም ተምሳሌት የሆነውን በዓል ሕዝቦች በአንድነት ከማክበር ባለፈም ፍቅራቸውንና መልካም ምኞታቸውን የሚለዋወጡበት ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

የመስቀል በዓል ሰዎችን የሚያቀራርብ የፍቅርና የመተባበር ተምሳሌት ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ይህንንም ቀልብ የሚሰብ በዓል ለማክበር በርካታ ቱሪስቶች ታድመዋል። ይህም ለሀገሪቱ ገፅታ ግንባታ ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ሃላፊዋ ገልጸዋል።

አዲስ አበባን እንደስሟ አዲስና ውብ ለማድረግ የተሠሩት ሥራዎች ለሕዝባችን ኩራት ለቱሪስቶች ኩራት ነው ብለዋል።

የበዓሉ ተሳታፊዎች በሃይማኖታዊ አልባሳት በመድመቅ በዓሉን ለመታደም ለመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች ባህላችንን ሊያስተዋውቁ ይገባልም ነው ያሉት።

በዓሉን ስናከብር የጥልና መለያየት መንፈስ በማስወገድ፣ እርስ በእርስ በመዋደድና በመተሳሰብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸው፤ ከተማ አስተዳደሩ የበዓላት እሴታቸውና ትውፊታቸው ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፉ በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

# “መስቀል በዓልን የምናከብረው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዕድላቸው መዳን ነው ሲል ይገልጻል ብለዋል።

በከፍተኛ ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት የምናከብረው የቅዱስ መስቀል በዓልም የመንፈሳዊ እና ቁሳዊ አካላት ግጭት የፈጠረው ክስተት ነው ያሉት ፓትሪያርኩ፤ መንፈሳዊው ሰው ከመስቀሉ በቀር ከፍዳ ኃጢአት እድንበታለሁ የምለው ሌላ ትምክት የለኝም ብሎ የመስቀሉን ዘላቂ አዳኝነትን ከፍ አድርጎ እንደሚዘምር ገልጸዋል፡፡

ቁሳዊው ሃይል ባለው አቅም ሁሉ ተንቀሳቅሶ መስቀሉን ከገጸ ምድር በማስወገድ በእሱ ላይ የተመሠረተውን አስተምህሮና እምነት እንዳይነሣም እንዳይወሳም በማሰብ መቅበሩን አንስተዋል፡፡

ቁሳውያን መስቀሉን ቢቀብሩትም የመስቀሉን ቃል ሊቀበሩ አለመቻላቸውን ገልጸው፤ የመስቀሉ ቃል ቁሳዊ ሳይሆን መንፈሳዊ፣ ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ፣ ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ፣ ሠብዓዊ ሳይሆን መለኮታዊ፣ ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ በመሆኑ ቁሳዊ የሆነው ዕፀ መስቀል ቢቀበርም እሱ የተሸከመው ቃለ ድህነት በረቂቁ የሰው አእምሮ ተቀርጾና ተዘግቦ ስለሚኖር ተቀብሮ ሊቀር አልቻለም ነው ያሉት።

በሂደትም ያልተቀበረው የመስቀሉ ቃለ ድህነት በንግሥት ዕሌኒ አእምሮ ውስጥ የእምነት ኃይል የተቀበረውን ዕፀ መስቀል በዛሬው ዕለት ከጥልቅ ጉድጓድ አውጥቷል። በዚህም አሸናፊነቱን አረጋግጧል፣ ዛሬ የምናከብረው በዓልም ይኸው ኃይለ እግዚአብሔር ለማሰብና በሱ ያለንን እምነት ለማስጠበቅና ቃለ ድህነቱን ለማሥረጽ ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

በዓለ መስቀሉን ከማንኛውም ክፍለ ዓለም በተለየ ሥነ ሥርዓት ብናከብርም የመስቀሉ ሰላም ግን በሀገራችንና በሕዝባችን እየተነበበ አይደለም ብለውም፤ ይህንን ለማስገንዘብ የሚተላለፈው መልእክትም እየተደመጠ አይመስልም፤ የመስቀሉ ቃል ማለት ሰዎች በነፍሳቸውም ሆነ በሥጋቸው የተሟላ ደህንነት ያግኙ ማለት ነው ብለዋል።

የመስቀሉ ቃል ማለት ሰዎች በዚች ምድር በእኩልነት በአንድነት በመተጋገዝ በመረዳዳት በፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በሰላም በፍቅር በስምምነት በመተባበር ይኑሩ ማለት መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

ይህንን የመስቀል ቃል ዓለም ብትቀበለው ኖሮ በየጊዜው እያንዣበበባት ያለው ስጋት ሁሉ ቦታ አይኖረውም ነበር ያሉት ፓትሪያሪኩ፤ አሁንም በመስቀሉ ስም ለዓለም ሕዝብም ሆነ ለሀገራችን ዜጎች ሁሉ የምናስተላልፈው ዐቢይ መልእክት የመስቀሉ ቃል ሁላችንንም በእኩልነትና በፍቅር የሚያስተናግድ ነውና እሱን እንቀበል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

# “እኛ ኢትዮጵያውያን ከተደመርን ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በለኮስን ጊዜ፤ እንደየባህላችን የመስቀልን በዓል ለማክበር በቤተሰብና በማኅበረሰብ ደረጃ በተሰባሰብን ጊዜ ኢትዮጵያን እናስባትም ብለዋል፡፡

የሁላችንም ዕሴቶች፣ ባህሎች፣ ወጎች፣ አቅሞች፣ ጸጋዎች፣ ሀብቶች፣ ቋንቋዎች እና ታሪኮች ተደምረው ኢትዮጵያን ታላቅ፣ የበለጸገችና የተከበረች ሊያደርጓት እንደሚችሉ እናስብ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ የእነዚህ ሁሉ ድምር መሆኗን እና ከድምሩም በላይ መሆኗንም እናስብ ብለዋል፡፡

ደመራውን እያሳየን ለልጆቻችን ከሃይማኖታዊና ባህላዊ ትርጉሙ በተጨማሪ “እኛ ኢትዮጵያውያን ከተደመርን እንደ ደመራው ብርቱ እንሆናለን፤ እንደደመራው ከፍ ብለን እናበራለን” በሏቸው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገለፃ፤ የመስቀል በዓል የሕልም ጉልበት የታየበት በዓል ነው፡፡ ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉን ለማውጣት ባለመቻበት ጊዜ መንገዶች ሁሉ ዝግ ነበሩ፡፡ ነገሮች ሁሉ አስቸጋሪ ነበሩ፡፡ ማንም በማያስበው ጊዜ፤ አይቻልም አይሞከርም በሚባልበት ወቅት፤ አንድ ቀን፤ ፈጣሪዋ ሲፈቅድ፤ መስቀሉን ከተቀበረበት ሥፍራ ለማውጣት ሕልም ነበራት፡፡ ከብዙ ውጣ ውረዶች በኋላ መስቀሉን ከተቀበረበት ሥፍራ ለማውጣት በቃች፡፡

በመሆኑም ደመራ ለሚታገል፤ ተስፋ ለማይቆርጥና እስከ መጨረሻው ለሚጸና ሰው ሕልሙ አንድ ቀን እውን እንደሚሆን የሚያሳይ ትእምርት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

# “የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደ ፕራንክ ገለጻ፤ በአዲስ አበባ እና አካባቢዋ የተሠሩ የልማት ሥራዎችን ተመልክቻለሁ። በዚህም ኢትዮጵያ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት እያስመዘገበች ነው።

በዓሉ ኢትዮጵያውያን አንድነታቸውንና ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውን የሚገልጹበት እንደሆነ መረዳቱን የገለፀው ፕራንክ፤ ስለመስቀል ደመራ በዓል ከጓደኞቹ ሰምቶ እንደመጣና ከጠበቀው በላይ አስደሳች ሆኖ ማግኘቱን ጠቁሟል።

ከቱርክ የመጣችው ግዩልዳን አምቢን በበኩሉዋ፤ በኢትዮጵያ የመስቀል በዓልን፣ የአክሱም ሃውልትን፣ ላሊበላንና ሌሎች አብያተ-ክርስትያናትን ለመጎብኘት መምጣቷን በመግለፅ፤ በአዲስ አበባ የተከበረው የደመራ በዓል ከጠበቀችው በላይ ደማቅና አስደሳች መሆኑን ተናግራለች።

ግዩልዳን አምቢን፤ በመስቀል ደመራ በዓል ላይ ባህላዊ አልባሳቶች፣ መዝሙሮች፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር ታሪካዊ ዳራ መመልከት አስደሳች መሆኑን ነው የገለጹት።

ባዩት ሃይማኖታዊ ሥርዓት እጅጉን መደሰታቸውን ያነሱት ግዩልዳን አምቢን፤ ኢትዮጵያ እንደሚነገረው ሳይሆን ፍፁም ሰላማዊና ኢኮኖሚዋን በፍጥነት እያሳደገች መሆኑን እንደተመለከቱ ተናግረዋል።

“በኢትዮጵያ ያለው የክርስትና እምነት በእጅጉ ይለያል” በማለት ባዩት ነገር መደሰታቸውን የተናገሩት የመስቀል በዓልን ለመታደም ከቱርክ የመጡት ሴሁን ካርታ ናቸው።

ሴሁን ካርታ በመስቀል በዓል አከባበር ላይ በርካታ ወጣቶችን መመልከታቸውና ይህም ለበዓሉ የተለየ ድምቀት መስጠቱን ነው የተናገሩት።

የመስቀል ደመራ በዓል ሁሉም ሊያከብረው የሚገባና አስደማሚ ሃይማኖታዊ ትውፊቶችን የያዘ መሆኑን በመግለፅ፤ ወደሀገራቸው ሲሄዱም በሚገባ ለማስተዋወቅ ዝግጁ መሆናቸውን አመላክተዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# የወጣቶች ተሳትፎ በአደባባይ በዓላት

**ሰሚራ በርሀ**

በሀገራችን በአደባባይ በርከት ያለ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች በጋራ ተሰብስበው በሕብረት ከሚያከብሯቸው ሀይማኖታዊ እና ባሕላዊ የታሪክ ዳራ ያላቸው በዓላት የአዲስ ዓመትን ተከትለው በዚህ የመስከረም ወር ላይ ይከበራሉ። የመስቀል ደመራ በዓል በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ በአደባባይ የሚከበር አንደኛው በዓል ሲሆን ሀይማኖታዊ ዳራውን ተከትሎ በየዓመቱ በጉጉት እና በድምቀት ይከበራል።

ባሕላዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ደግሞ የመስቀል በዓል በደቡቡ የሀገራችን ክፍል የዘመን መለወጫ በዓል ሲሆን ወላጆች በናፍቆት በተለያየ ቦታ ያሉ ልጆቻቸውን የሚጠብቁበት ልጆችም ለዓመት ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ ለቤተሰቦቻቸው ስጦታ ይዘው ከያሉበት በዓሉን አስታከው የሚሰባሰቡበት ነው። በመስከረም ወር በደማቅ ሁኔታ የሚከበረው ሌላኛው በዓል እንዲሁ የኢሬቻ በዓል ነው። ባሕላዊ ትውፊት በጠበቀ መልኩ የበዓሉ ተሳታፊዎች ወደ አደባባይ በመውጣት ያከብሩታል። የመስቀል ደመራ በዓል እና የኢሬቻ በዓል ኢትዮጵያውያን በጋራ ከቤታቸው ወጥተው በአደባባይ የሚያከብሯቸው ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ጎብኚዎችን ጭምር ወደ ሀገራችን እንዲመጡ የሚጋብዙም ጭምር ናቸው ።

በዚህ በዓል ወቅት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ሚና ምን መምሰል ይገባዋል ፣ በዓሉን እንደከዚህ ቀደም ታሪኩን እና ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ በሰላም ተከብሮ ይጠናቀቅ ዘንድ ወጣቶች የሚያደርጉትን ዝግጅት በተመለከተ ከአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር ዋና ጸሀፊ ከሆነው ወጣት ይሁነኝ መሀመድ ጋር ቆይታ አድርገናል። ማህበሩ ከተመሰረተ 26 ዓመታትን ያስቆጠረ መሆኑን የገለጸው ወጣቱ ‹‹ሀገራችን ካሏት ሀይማኖታዊም ሆኑ ባሕላዊ ትውፊት ያለው አንዱ በዓል የመስቀል ደመራ በዓል ሲሆን የኢሬቻ በዓልም እንዲሁ ሌላኛው ነው። እነዚህን በዓላት እንደ ሀገር እና እንደ ሕዝብ ብቻም ሳይሆን በዩኔስኮ የተመዘገቡ ጭምር በመሆናቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት ያገኙ ጥበቃ የሚደረግላቸው ናቸው።›› እነዚህን በዓላት ታዲያ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ ያደረጋቸው የራሳቸው የሆነ መለያ ያላቸው በመሆኑ በትልቅ ትኩረት እና ከፍታ ይዘታቸውን እንደጠበቁ እንዲከበሩ ማድረግ የሁሉም ማኅበረሰብ ኃላፊነት መሆኑን ዋና ጸሀፊው ወጣት ይሁነኝ ገልፆል ።

በእነዚህ በዓላት ላይ ወጣቶች የሚያከብሩበት መንገድ ትኩረትን የሚስብ ሲሆን በበዓሉ እለት ወጣቶች የሚኖራቸው ሚና ከፍ ያለ እንደሚሆንም አክለው ገልጸዋል። ‹‹ወጣቶች የትላንት ታሪክን ወደ ዛሬ የሚያሻግሩ፣ የዛሬን ደግሞ መሰረት ሆነው ጠብቀው አቆይተው ለነገው ትውልድ የሚያስተላልፉ ናቸው።›› በመሆኑም በዚህ ሂደት ወጣቶች የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ማኅበሩ ማኅበራዊ ጉዳይ ብሎ ባስቀመጠው ክፍል ሀገራዊ እና ዓለምአቀፋዊ ጉዳዮች ባለፈ ወቅታዊ ኩነቶች ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል።


በ2017 ዓ.ም ተከብሮ በዋለው የደመራ ስነ-ስርዓት እንዲሁም በቀጣይ ቀናት ለሚከበረው የኢሬቻ በዓል በድምቀት ተከብሮ እንዲውል ከእለቱ አስቀድሞ እና በበዓሉ እለት የሚያስተባብሩ በርካታ ወጣቶችን ማኅበሩ ማደራጀቱን ወጣት ይሁነኝ ይገልጻል። ‹‹ለመስቀል የደመራ በዓል ከመድረሱ አስቀድሞ የሚከበርበትን ቦታ ከማጽዳት እና ለበዓሉ እለት ዝግጁ ከማድረግ ጋር ተያይዞ የእምነቱ ተከታዮች ብቻ ሳይሆኑ እንደ ኢትዮጵያዊ ሁሉም ወጣት የሚሳተፍበት ነው። የመስቀል ደመራ በዓል በርካታ ቁጥር ያለው ምዕመን የሚሳተፍበት እንደመሆኑ ከሚመለከታቸው የመንግስት የሰላምና ጸጥታ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ የጸጥታ ስጋት ሳይኖር እንዲከበር እናደርጋለን።›› በዚህም በዓሉ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የእምነቱ ተከታዮች ወደ አደባባይ በመውጣት የሚያከብሩት ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማም በመስቀል አደባባይ በርካታ ቁጥር ያላቸው የእምነቱ ተከታዮች እና በዓሉን ለመታደም የሚመጡ እንግዶች ባሉበት ይከበራል። ማኅበሩ በእለቱ በዓሉን ለማክበርና ለማድመቅ ወደቦታው ከሚሰባሰቡ የተለያዩ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት የእምነት ተቋማት፣ የተለያዩ ደብሮች የሚመጡ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሀይማኖት አባቶች ጋር የበዓሉ አከባበር ምን መመስል ይገባዋል የሚለውን ውይይት አድርገዋል።





> **ሀገራችን ካሏት ሀይማኖታዊም ሆኑ ባሕላዊ ትውፊት ያለው አንዱ በዓል የመስቀል ደመራ በዓል ሲሆን የኢሬቻ በዓልም እንዲሁ ሌላኛው ነው**





የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር ከተመሰረተ 26 ዓመት ማስቆጠሩን የገለጸው ዋና ጸሀፊው ከማኅበሩ ውጪ ያሉ ወጣቶችን ጭምር ባሳተፈ መልኩ ውይይት በማድረግ በዓሉ ተከብሮ እንዲያልፍ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። « በመስቀል አደባባይ ከሚከበረው በዓል እንዳለ ሆኖ በየአከባቢው ትልቅ ቁጥር ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች በጋራ ሆነው ያከብራሉ። በየአከባቢው በዓሉ በሰላም ተከብሮ እንዲያልፍ የሚሳተፉ ወጣቶቻችንን ደልድለናል።›› የአከባቢውን ሰላምና ጸጥታ የሚያናጉ በየአከባቢያቸው እንደ ወጣት ይሁነኝ ገለጻ ይህንን የመስቀል ደመራ በዓል እና ኢሬቻ የመሳሰሉ የአደባባይ በዓላት በሚከበሩበት ጊዜ ወጣቶች የከተማዋ ሰላምና ጸጥታ በተጠበቀ መልኩ እንዲከበር ከበዓሉ ጋር ተያይዞ አላስፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች እንዳይኖሩ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ሚናቸውም ከፍ ያለ ይሆናል በማለት ገልጸው፤ ይህ እንቅስቃሴም ሆነ የወጣቶች ተሳትፎ ግን የመንግስትን ሚና በመተካት ሳይሆን ነገር ግን ሰላምና ጸጥታ በተረጋገጠባት ከተማ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች በቀጣይ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን፣ ማኅበራዊ ተሳትፏቸው እና ፖለቲካዊ ተሳትፏቸው የሚያሳድጉበት ነው።

ደመራ በሚደመርባቸው አካባቢዎች ከኤሌክትሪክ ቦታዎች ተቀጣጣይ ነገሮች የራቀ እንዲሆን አደጋ እንዳይፈጠር እንዲሁም ከአዲስ አበባ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ጋር በጋራ በመሆን ይሰራሉ ።

ሌላኛው ከዚህ በኋላ በቅርብ ቀናት ውስጥ በድምቀት የሚከበረው የኢሬቻ በዓል ነው። ‹‹የኢሬቻ በዓል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከተማችን አዲስ አበባ በድምቀት የሚከበር በዓል ነው። በመሆኑም የኢሬቻ በዓል የሚከናነወንበትን ቦታ በማጽዳት ለበዓሉ ዝግጁ እንዲሆን የማድረግ ስራዎችን እንሰራለን።›› ያለው ወጣት ይሁነኝ የበዓሉ ተሳታፊዎች ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ አጎራባች በዓሉን ለመታደም የሚመጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ወጣቶች ወደ ከተማዋ የሚመጡበት በመሆኑ ማኅበሩ በሚያሰማራቸው ወጣቶች በዓሉን ለመታደም ወደ ከተማዋ የሚመጡ እንግዶች ሳይቸገሩ ወደሚከበርበት ቦታ እንዲደርሱ የማመላከት ፣ በዓሉ የሚከበርበትን ዓውድና ዐላማ በጠበቀ መልኩ እንዲከበር ከሸገር ከተማ አስተዳደር ፣ ከኦሮሚያ ክልል አስተዳደር ጋር በመቀናጀት በዓሉ በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ እንዲያልፍ እየሰሩ መሆናቸውን አክሏል።

እነዚህ ሁለት በዓላት በዩኔስኮ የተመዘገቡ መሆናቸው ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ጎብኚዎች በዓሉን ለመመልከት ለመታደም ወደ ሀገር የሚገቡበት በመሆኑ እንግዶችን ተቀብሎ ከማስተናገድ አንጻር ምን ስራዎች በማኅበሩ በኩል ይሰራል ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄ ዋና ጸሀፊው ይህን ምላሽ ሰጥተዋል። « በዓላትን ለመታደም ወደ ሀገራችን የሚመጡ እንግዶችን ባሰቡት መልኩ በዓሉን እንዲያከብሩ እና ማየት የሚፈልጉትን አከባበር እንዲያዩ ማድረግ ዋነኛው ስራ ነው ፤ ምክንቱም በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲመዘገብ ያደረገው የበዓሉ አከባበር ስለሆነ ከዛ በመቀጠል፣ ንብረታቸው ባልሆኑ አካላት እንዳይወሰድ የማድረግ ስራ እንሰራለን ፡ በኢሬቻ በዓል የተለያዩ ኅብረተሰቦች ከክልል ስለሚመጡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ከሚሰጡ ሆቴሎች፣ የንግድ ማዕከላት ጋር ካለፈው ዓመት ልምድ በመነሳት እና የነበሩ ክፍተቶችን በማስተካከል እንዲስተናገዱ በማድረግ እኛም ደግሞ መተላለፊያ ቦታዎች ላይ በመገኘት ቦታዎችን በመጠቆም፣ በክብረ በዓሉ ላይ የራሳችንን አስተዋጽኦ እናደርጋለን። »

የኢሬቻ በዓል በዓሉን በሚያከብሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለዓመታት እየተከበረ እና ዛሬ የደረሰ በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን አግኝቷል። ከዚህ ቀደም ባለፉት ዓመታት የነበረው አከባበር በተሳካ ሁኔታ ተከብሮ ያለፈ መሆኑን ጠቅሰው በዘንድሮ ዓመትም ለዚህ በዓል በድምቀት መከበርም ከሚሰሩ የመንግስት አካላት ጋር ማኅበሩ ተቀራርቦ ለመስራት ዝግጁ መሆኑንም የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር ዋና ጸሀፊ ይሁነኝ መሀመድ ገልጸዋል።

ሀገራችን በአሁን ሰዓት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እና ሌሎች ጥያቄዎች የውስጥም ሆኑ የውጭ ከሚመጡ ችግሮችን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች ያለው የማህበሩ ዋና ጸሀፊ እንዚህን ችግሮች ለመፍታት እንደ መስቀል ደመራ በዓል እና ኢሬቻ በዓላት የሚፈለጥሩልንን እድሎች በመጠቀም አንድነታችንን፣ ሕብረብሄራዊነታችንን፣ ውስጣዊ ሰላማችንን መጠበቅ እንችላለን ያሉ ሲሆን ‹‹እነዚህን በዓላት እና ሁነቶች በመጠቀም ያልተገቡ ተግባራትን የሚፈጸሙ ክፍሎች መጠቀሚያ የሚያደርጉት የወጣቱን ክፍል በመሆኑ ወጣቶች ይህንን ተረድተው ለራሳቸው በመቆም እና መሰል ድርጊቶችን በመከላከል ራሱን እና አካባቢውን በመጠበቅ ኃላፊነታቸውን በመወጣት እነዚህን እና ሌሎች ሀይማኖታዊም ሆኑ ባኅላዊ ትውፊት ያላቸውን በዓላት በሰላምና በድምቀት ማክበር እና አንድነታችንን ማጠንከር እንችላለን ። ›› በማለት አዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር ዋና ጸሀፊ ወጣት ይሁነኝ መሀመድ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ተቀናጅቶ መስራትን የሚጠይቀው የከበሩ ማዕድናት ልማት



> **የከበሩ ማዕድናትን ጥራት ለማወቅ በማንኛውም ኬሚካል ላብራቶሪዎች የሚመረመሩ አይነት ስላልሆነ ማዕድን የጥራት ደረጃውን ለማወቅ የሚያስችሉ የራሳቸው መለኪያዎች አላቸው:: ዝም ብሎ በማየት ብቻ ግን የጥራት ደረጃቸው ማወቅ አይቻልም**

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ ከሚገኙ ማእድናት መካከል የከበሩ ማዕድናት ይጠቀሳሉ። ማእድናቱ የከበሩ ለመባላቸው አንዱ ምክንያት የሚገኙበት ሁኔታ ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ማዕድናቱ በበቂ ሁኔታ እንደልብ የማይገኙ መሆናቸው የከበሩ ሊያሰኛቸው እንደቻለም ይናገራሉ።

ከእነዚህ ማእድናት መካከል ሳፋየር፣ ሩቢ፣ ኤምራልድ፣ ኦፓል፣ ጃስበር፣ ኦብሲዲያን፣ ጋርኔት፣ አሜቲስት እና ሲትሪን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ማዕድናት በአብዛኛው ለመዋቢያ ጌጣጌጥነት የሚውሉ ናቸው።

የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን የጌጣጌጥ ክፍል ሥራ አስኪያጅ አቶ ዘካሪያስ ፍቃድ ስለከበሩ ማዕድናት ሲገልጹ፤ ከሌሎች ማዕድናት አንጻር ሲታዩ የከበሩ የተሰኙበት ዋንኛ ምክንያት አገኛኘታቸው እንደሆነ ያስረዳሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የከበሩት ማዕድናት እንደልብ በበቂ ሁኔታ አይገኙም። ይህም የከበሩ ተብለው እንዲለዩ አድርጓቸዋል። የከበሩ ማዕድናት ሁለት አይነት ናቸው፤ የከበሩ (precisions) እና በከፊል የከበሩ (semi precisions) ይባላሉ። በከፊል የከበሩ ማዕድናት ከሌሎች የከበሩ ማዕድናት አንጻር ሲታዩ በተሻለ መልኩ በብዛት ሊገኙ ይችላሉ። የከበሩ የሚባሉት ማእድናት ግን የመገኘት እድላቸው እጅግ አነስተኛ ነው።

በከፊል የከበሩ (semi precisions) ከሚባሉ ማዕድናት መካከል ጃስበር፣ ጥቁር ባልጭ /ኦብሲዲያን/፣ ጋርኔት፣ አሜቲስት፣ ሲትሪን ይገኙበታል። የከበሩ የሚባሉት ደግሞ በአንጻራዊነት የመገኘት እድላቸው እጅግ አነስተኛ የሆነው እንደ ሳፋየር፣ ኤምራልድ፣ ኦፓል አይነቶቹ ናቸው።

ኢትዮጵያ የተለያዩ አይነቶች የከበሩ ማዕድናት እንዳሏት ጠቅሰው፣ እነዚህም ማዕድናት በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች እንደሚገኙ አቶ ዘካርያስ ይናገራሉ። እስካሁን ባለው ግኝት በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች በተለይ በኦሮሚያ ክልል፣ በአማራ ክልል እና በደቡብ ክልል እንዲሁም በሰሜን የአገሪቷ ክልል ላይ ይገኛሉ። ለአብነትም በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙት የከበሩ ማዕድናት ውስጥ አንዱ ኤምራልድ ነው። በክልሉ የሚገኘው ኤምራልድ ሌሎች ቦታ ላይ ከሚገኙ የተሻለ ጥራት አለው። ሩቢ እና ሳፋየር የሚባሉት የከበሩ ማዕድናት ደግሞ በሰሜን የአገሪቷ ክፍል በተለይ በትግራይ ክልል በስፋት ይገኛሉ። ኦፓል የተሰኘው ማዕድንም እንዲሁ በአማራ ክልል በደቡብ ወሎ ዞን ደላንታ አካባቢ በስፋት እንደሚገኙ ይገልጻሉ።

አቶ ዘካርያስ እንዳብራሩት፤ እነዚህ ማዕድናት ከምንለይበት ዋና መንገድ አንዱ በአገኛኘታቸው ነው። ተገኝተውም ደግሞ የጥራት ደረጃቸው በራሱ የተለያዩ መሆኑ ሌላኛው ነው። ለአብነት ኦፓል የተሰኘውን ማዕድን ብንመለከት የሰሜን ሸዋ እና የደላንታ ኦፓል በመባል ይታወቃል። እነዚህ በሁለቱ የኦፓል አይነቶች መካከል ሰፊ ልዩነት ያለ ሲሆን፤ በተለይ የደላንታው ኦፓል በአውስትራሊያ ከሚገኘው ኦፓል እኩል ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። አሁን ላይ እየወጡ ያሉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ደግሞ የጥራት ደረጃቸው ከአውስትራሊያው ኦፓልም የበለጠ መሆኑን ነው። በዚህ የተነሳ የደላንታው ኦፓል ዋጋ ከሌሎች አንጻር ከፍ ያለ ነው::

ሌሎች አካባቢዎች የተወሰኑ የኦፓል አይነቶች አሉ። ለአብነትም ፋየር ኦፓል የተሰኘው በአፋር አካባቢ ይገኛል። ኦፓል በተለያዩ ቦታዎች የሚገኝ ሲሆን እንደ የኦፓሉ አይነት ደረጃውና የጥራቱም ይለያያል። እነ ሳፋየር፣ ሩቢ አይነት ማዕድናት ደግሞ ከኦፓል እጅግ ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው መሆኑን አቶ ዘካርያስ አስገንዝበዋል።

አገሪቱ እነዚህ መሰል የከበሩ ማዕድናት ቢኖራትም ግን ማዕድናቱ አሁንም ድረስ እየተመረቱ ያለበት መንገድ ትክክል እንዳልሆነ የሚጠቆሙት አቶ ዘካርያስ፤ በባህላዊ መንገድ ስለሚመረትና ቴክኖሎጂን የመጠቀም እድሉ ውስን መሆኑንም ለዚህ እንደዳረጋቸው ያስረዳሉ። እስካሁን ድረስ ማዕድናቱን የሚመረቱ እንደዶማ፣ ዲጅኖ ያሉ የተለያዩ ባህላዊ መሳሪያዎች በመጠቀም እንደሆነ ይገልጻሉ። ባህላዊ የአመራረት ሂደት ተጠቅመን ሲመርቱ ደግሞ ማዕድኑ ሊመታ ስለሚችል የመሰባበርና የመሰነጣጠቅ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ ማዕድኑ ያለው የጥራት ደረጃ እንዲወርድ ስለሚያደርገው በገበያ ላይ ያለው ተቀባይነት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ማዕድናቱ ከማምረቱ በኋላ በጥሬው ለገበያ ከማቅረብ ይልቅ እሴት ማከል ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ አጽኖት ሰጥተው ይናገራሉ። ቀደም ባሉት ጊዜያት አንድ ችግር የነበረው ማዕድኑ ምንም አይነት እሴት ሳይታከልበት በጥሬው መውጣት እንደነበር አንስተዋል። በሕገወጥ መንገድ ድንበር አልፈው የሚሄዱበት ሁኔታዎች መኖሩን ጠቅሰው፤ ማዕድኑ በጥሬ መላኩ እንዳለ ሆኖ በተጨማሪ ደግሞ በሕገወጥ መንገድ ከሀገር እንዲወጣ መደረጉ እንደሀገር ኪሳራ ሲያስከትል የቆየ መሆኑን ይገልጻሉ። አሁን ላይ መንግሥት አሰራር ሥርዓቱን በደንብ ስላስተካከለ ቁጥጥሩ በደንብ እየተጠናከረ መምጣቱ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የከበሩ ማዕድናት ላይ እሴት ማከል ሲባል ለመዋቢያ ጌጥነት በሚውሉ መልኩ ማዘጋጀት ነው። በተለይ ለሰው ልጅ ውበት የሚውሉ ጌጣጌጦችን ለመስሪያነት ይወላሉ። የአንገት ጌጥ፣ የጆሮ ጌጥ፣ የእጅ አምባር፣ እና የጣት ቀለበት እና የመሳሰሉት አገልግሎት ላይ ውለው ውበትን ይሰጣሉ። ማዕድናቱ በዚህ መልኩ እሴት ታክሎባቸው አገልግሎት ላይ ከዋሉ የሚቀሩ ሌሎች ተረፈ ምርቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚያ ተረፈ ምርቶች ውድ ስለሆኑ በአግባቡ በመጠቀም ለሌሎች ነገሮች ማስዋቢያነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለምሳሌ ለተለያዩ ለዲኮር ሥራዎች፣ ለፈርኒቸር ውበት፣ ለሌዘር ፋብሪካዎች እና መሰል አገልግሎቶች ሊውሉ ይችላሉ። የከበሩ ማዕድናት ላይ እሴት በማከል መስራቱ እንደሀገር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል ::

ማዕድናቶቹ ከመመረት ጀምሮ ጥራታቸው የጠበቁ እንዲሆኑ የሚሰሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው። በተጨማሪም ከእነዚህ ማዕድናት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሕገወጥነት ሕጋዊ መንገድ እንዲከተል ለማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራትን ይጠይቃል የሚሉት አቶ ዘካሪያስ፤ ለአብነትም የአውስትራሊያን ተሞክሮ ያነሳሉ። አውስትራሊያዊያን በከበሩ ማዕድናት ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደአገር ትልቅ አጀንዳ አድርገው ብዙ ሥራዎች መስራታቸው ይናገራሉ::

በተለይ ራሳቸው የሚያመርቱትን ኦፓልን የተሻለ ጥራት እንዳለው አድርገው በማስተዋወቅ በማቅረብ ብራንዱ ከፍ ብሎ እንዲታይ አድርገዋል። ሃቁን ስንመለከት ግን የኢትዮጵያ ኦፓል ከአውስትራሊያን የተሻለ ሆኖ ሳለ ማዕድናት የማስተዋወቅ ላይ ውስንነት ስላለ የተሻለ መሆንን ማሳየት አልቻልንም። ለዚህም በማዕድናቱ ዙሪያ ያለ የግንዛቤ ውስንና ፕላትፎርሙ አለመኖር በምክንያትነት ይጠቅሳሉ።

በአገሪቷ ያሉ ማዕድናት ለዓለም የማስተዋወቅ ሥራ እምብዛም ያልተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ እንደሀገር ያሉት እንደ ኦፓል ያሉ የከበሩ ማዕድናት እሴት በማከል ለዓለም ማስተዋወቅ የሚመለከታቸው ሁሉ ሊሰሩበት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

እንደሀገር 40 በላይ የተለያዩ የከበሩ ማዕድናት ያሉ ቢሆንም ግን ምን ያህሉ ላይ በደንብ ተሰርቷል የሚለው በደንብ መታየት አለበት የሚሉት አቶ ዘካርያስ፤ አሁን ላይ ዋንኛ እሴት ከማከሉ ላይ መስራት ጎን ለጎን ማምረቱ ላይ ትኩረት በመስጠት የሚያመርቱ አምራቶች አቅም ማሳደግና ባለሙያው ማፍራት ላይ ሊሰራ ይገባል ይላሉ።

እንደ አቶ ዘካርያስ ገለጻ፤ እንደሀገር የከበሩ ማዕድናት ብዙ ትኩረት የተሰጣቸው ስላልሆነ እሴት ለማከል እንኳን ብዙም የሚባል የተማረ ሰው አልነበረበትም። እስካሁንም ድረስ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ደረጃ እንኳን ሙያዊ ስልጠናም ቢሆን እየተሰጠ ያለው አማራ ክልል ብቻ ነው። የእሴት ማከል (ላፒደሪ) ሥራ የከበሩ ማዕድናት የመቁረጥ፣ የማለስለስ እና የማስዋብ ሥራን የተለያዩ ድርጅቶች በግል በተወሰነ መልኩ እንቅስቃሴዎች እያደረጉ ነው። "መንግሥት ግን ትኩረት ሰጥቶት እየተሰራ ያለው በአማራ ክልል ብቻ ነው። በሌሎች ክልል የእሴት ማከል (ላፒደሪ) ባለሙያ ብንፈልግ ላናገኝ እንችላል። ይህም ዘርፉ ገና ያልተነካና ብዙ እንዳልተሰራበት በመሆኑ ብዙ ሥራን የሚጠይቅ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም እሴት ከማከሉ ጀምሮ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት መስራት እንዳለበት አምናለሁ›› ይላሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የከበሩ ማዕድናትን ጥራት ለማወቅ በማንኛውም ኬሚካል ላብራቶሪዎች የሚመረመሩ አይነት ስላልሆነ ማዕድን የጥራት ደረጃውን ለማወቅ የሚያስችሉ የራሳቸው መለኪያዎች አላቸው። ዝም ብሎ በማየት ብቻ ግን የጥራት ደረጃቸው ማወቅ አይቻልም:: ለምሳሌ አንድ ኤምራልድ ብንወስድ በጥሬ ከሚላክ ይልቅ እሴት ቢታከልበትና ቢቀርብ የሚያስገኘውም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። አሁን ላይ ትንሽ ከሚሰራ ሥራ አንጻር እንኳን ሲታይ ጥሩ የሚባል የገበያ እንቅስቃሴ በመኖሩ ታይታል። በደንብ ቢሰራበት ደግሞ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ምንጭ ሆኖ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ያስችላል። በዚያው ልክ ደግሞ የውጭ ገበያ ፍላጎት እየጨመረ ፈላጊዎች እየበዙ ይመጣሉ::

የማዕድናት ምርመራ ላይ ከባለሙያዎች እጥረት ጋር ተያይዞ ውስነቶች አሉ ያሉት አቶ ዘካርያስ፤ አንዱ ከሰልጠና ጋር ተያይዞ ትምህርቱ የሚሰጡ ተቋማት አለመኖር መሆኑን ይገልጻሉ። እነዚህ ችግር በመፍታት ለብረትነክና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት ላይ በሰፊው ሲሰራ እንደነበር ይገልጻሉ። ማዕድናት ላይ እሴት የማከሉ፣ የመመርመሩ እና ጥራት እንዲጠብቁ የማድረግ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል። ለምሳሌ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ብንወስድ ግብዓት ሊውል የሚችል ማዕድን የኖራ ድንጋይ ነው። ይህ ድንጋይ ጥራቱ በሚገባ እስካልጠበቀ ድረስ፣ ማዕድኑ ትርጉም አይኖረውም። ለዚያም ነው ተመርምሮ የሚሰራው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዘካርያስ ገለጻ፤ የከበሩ ማዕድናት ምርመራ ከኬሚካል ላብራቶሪ የተለየ ነው። የተለያዩ መሳሪያዎች በመጠቀም በማረጋገጥ ይቻላል። እንደሌንሲ እና ሀርድነስ/ አይነት መሳሪያዎች መጠቀም የማዕድኑ የጥንካሬ ደረጃ መለየት ያስችላሉ። እንዲሁም ማዕድኑ ጥራት ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን እና ተፈጥሮአዊ ነው ወይስ አርተፊሻል የሚለውንም ለመለየት ይረዳሉ። አሁን ላይ በአብዛኛው በገበያ ላይ የከበሩ ማዕድናት ተብለው የሚቀርቡ ጌጣጌጦች የተፈጥሮ እና አርተፊሻሉ ቀላቅሎ የመሸጥ ሁኔታ ይስተዋላል። ይህ ደግሞ እንደሀገር ገጽታ የሚያበላሽ ስለሆነ ሰዎች እነዚህ ማዕድናት ለመለየት በጣም ይቸገራሉ። እነዚህ ማዕድናት ለማወቅ የሚጠቅሙ የተለያዩ መሳሪያዎች ያሉ ቢሆንም ምርመራ በጣም ውስንነት ስላለው በአብዛኛው በባለሙያ እገዛ በመለየት የሚሰራበት ሁኔታ ነው ያለው። ሆኖም ግን በባለሙያ የሚሰጠው ድጋፍ ግን በቂ ስላልሆነ ደግሞ በመሳሪያ የታገዘ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

በአገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የከበሩ ማዕድናትን በመሳሪያ ተጠቅመን እየቆረጥን እያለሰለስን ለተለያዩ ጌጣጌጦች ማዋልን መማር እንፈልጋለን የሚሉ ጥያቄዎች ከሕብረተሰቡ እየቀረቡ መሆናቸውን ይገልጻሉ። ይህም በዘርፉ ላይ ያለው ግንዛቤ እያደገ መምጣቱን ያሳያል ይላሉ። ስለዚህ በተለይ በዘርፉ ላይ ተሰማርተው እየሰሩ ያሉ ተቋማትም ሆኑ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በትብብርና በቅንጅት በመስራት የሚጠበቅባቸው መውጣት እንዳለባቸው አሳሰበዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ተፈጥሮ ጀርባን ባትሠራ ምን ነበር

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ተፈጥሮ ግን መሰሪ ናት..የማንደርስበትን ጀርባ ከኋላችን አስቀምጣ ከራሳችን ጋር ትንቅንቅ ውስጥ ያስገባችን። ጀርባዬ ላይ ሌላ ነፍስ ያለ ይመስለኛል..አርፌ እንዳልቀመጥ የሚያቅበዠብዠኝ ነፍስ። ከመላው ሰውነቴ ተለይቶ ጀርባዬ ላይ እንደእንሽላሊት የሚሄድ፣ የሚቧጥጥ፣ የሚያቅራራ፣ የሚውረገረግ ብል አለ..ላከው ስል የሚጠፋ። ደሞ እኮ ብቻዬን ሳለሁ በዝምታ ሰንብቶ ፕሮቶኮል የሚፈልግ ቦታ ላይ መንቃቱ ነው። ሸክ ብዬ ፍቅረኛዬን ላገኝ ወይም ደግሞ ለሆነ ትልቅ ጉዳይ ሰው መሀል ስገኝ ጠብቆ የሚበላኝ ነገር ነው የሚያስቆጣኝ። ከሰውነት ጋር አብሮ የተሰጠን የሆነ ነገር እማ አለ..እንደጀርባ ከኋላ አድብቶ እንከናችንን ሊገልጥ በስውር የሚከተለን፡፡

በሰውነት ላይ በፉክክርና በእኔ እበልጥ ጣውንታሞች ሆነው ጎራ የፈጠሩ ሁለት ሃሳቦች አሉ..

ሰው በስላሴ ሃሳብ ከአፈር ተሠራ...

ሰው በዝግመተ ለውጥ ከዝንጀሮ ወደሰውነት ተቀየረ.. የሚሉ፡፡

ዳርዊን ወይስ እየሱስ ማናቸው ናቸው ልክ? ብዬ አልጠይቅም። ፍጡርን ከፈጣሪ ጋር ማወዳደረወ ሆኖ አይደለም ሲታሰብ የሚነዝር ድርጊት ነው። እኔ ለእየሱስ አድልቼ በረጅም ዘመን ስልሳሌ የሚሆነኝን መርጫለው። በበኩር እማኝ ምስክር ሰውነቴን በጸጋ ተቀብያለው። ግን ጀርባ ላይ እከክ ከየት መጣ? ታላቅ ሃሳብ ውስጥ እከክ ምን ይሠራል? ከአፈር ተሠርተህ ድሮስ እንከን ላይኖርብህ ነው? የሚል መልስ መሳይ ሃሳብ አእምሮዬ ውስጥ በቀለ። ደግሞ ሌላ አደመጥኩ..‹አታብል..ከአፈሩ ሰሪው ይልቃል። ሰሪው አፈሩን የመረጠበት ምንም መሆናችንን በመናገሩ ውስጥ ሌላም ትርጉም አለው› የሚል። ሁለት የማላውቃቸው ጎራዎች በራሴ ውስጥ ግብ ግብ ፈጠሩ። ወደየትኛው እንደምወግን መላ ጠፋኝ፡፡

ሁለተኛው መንፈሴ በእልህ ንግግሩን ቀጠለ ‹ምንም ነው ያልከው አፈር የሕይወት ማህጸን ነው። ዘርተን የምንበላው በአፈር ነው። መነሻና መድረሻችን መሬት ነው። የሚበልጠው አብሯቸው እስካለ ድረስ ትናንሾቹ ባለሃይል ናቸው። አፈር የሕይወት ቀለም የሆነው በአስገኚው በኩል ነው። ጎልያድና ዳዊትን አስታውሳቸው..ዳዊት አፈር ነው..ጎልያድ ደግሞ ባለሞገስ..መቼም ማን የክብር ኒሻን እንዳጠለቀ ታውቀዋለህ። አየህ የሚበልጠው አብሮህ ሲሆን እንደዚህ ነው። በአፈር ውስጥ የእኔና የአንተ ሰው መሆን ሊገርምህ አይገባም። ልክ የማትሆነው የሚበልጠው አብሮህ ያልሆነ ጊዜ ነው። አንዳንድ ጊዜ አልመን እንዳንስታቸው ግዙፍ ጥላዎች በዙሪያችን ያንጃብባሉ.. ብዙሃን ፈርተው ሲያፈገፍጉ ደቂቃን ቀስታቸውን ይወረውራሉ..ወርውረውም አይስቱም..ይሄ የእኛ አቅም ሳይሆን የሚበልጠው ተራዳይነት ነው፡፡

የመጀመሪያው መንፈሴ..በዝምታ ተዋጠ፡፡

እኔ ውስጥ ሁለት ጎራ የመፈጠሩ ነገር በየትኛውም ነገር ላይ እርግጠኛ አለመሆኔን ጠቆመኝ። ሕይወት ሰፊ ናት ሳይገባኝ እንደገባኝ የተቀበልኩት ይኖራል..ገብቶኝም እንዳልገባኝ የሆንኩትም፡፡

ዝም ያለው መንፈሴ ግን እኮ ሲል አደመጥኩት..‹ግን እኮ አፈር ሕይወት ብቻ ሳይሆን ሞትንም ያበቅላል። አንተ ራስህ ይሄ ገብቶህ ነው የምትናገረው? የሕይወት እከክ ከአፈር ካልበቀለ ከየት መጣ ልትል ነው? አለው ሁለተኛውን መንፈሴን። አሁን ሲገባኝ ጠያቂና መላሽ ሆነው እኔን ወደእውነተኛ መንገድ ሊወስዱኝ የተቃረኑ መሰለኝ፡፡

‹አፈር የሕይወት መብቀያ ነው..አለመኖር በዚህ ስም አይጠራም እናም ከአፈር አልተነሳም። የሕይወት እከክ የሰው ልጅ በመኖር ውስጥ ከአፈር የጣለው ኋላም እሾህ ሆኖ በቅሎ ራሱን ያደማው እንጂ ተፈጥሮ ያበቀለው አይደለም። አንተ የምትለውን ያለመኖር እንክርዳድ የሰው ልጅ ራሱ ነው ዘርቶ ያጸደቀው› ሲል መለሰለት፡፡

ጠያቂው መንፈሴ ወደዝምታው አዘቅት ተመለሰ

አከሎም ‹ሰው ንጹህ ዘር ነው..ነገዱም ሀሳበ ሥላሴ ነው። ንጹህ ሃሳብ ውስጥ ብላሽ ታሪክ የለም..ዘራችን አንዱአምላክ ነው። ከምርጥ ሃሳብ ስር ካለ ዘር በቅለን አበባ መሆን ሲገባን በራሳችን ላይ የሃጢያትን እከክ ፈጠርን። ይሄ እከክ ብልና ጠዝጣዥ ሆኖ ከራሳችን ጸጉር እስከ እግራችን ጣቶች ድረስ ቅማልና ጮቅ ሆኖ መጣ። እከክ የሌለበት አካል የለንም። ምርጥ ዘራችንን በነውር ለውጠን ቤተመቅደስ ሰውነታችንን የባዕድ መፈንጫ አድርገናል። ራስ ለዘውድ አንገት ለድሪ መሆኑ ቀርቷል። ደረት ለግማድ፣ ክንድ ለአልቦ መሆኑ ዘበት ነው። ወለባና አሸከታቦቻችን የክብር ሥፍራ አጥተው በእከክ ተመንዝረዋል። ራሳችን ዘውድ መጫን ሲገባው የተባይ መናኸሪያ ሆኗል። ክብሮቻችን የሉም..

ጽንፍ የረገጡ ጥንድ መንፈሶቼን ለዝምታ ጥዬ ወደራሴ የጀርባ እከኬ ተመለስኩ። ጀርባ ባልተፈጠረ ከተፈጠረም ቧጠን ብንደርስበት ምናለ የሚለው ተቀዳሚ ምኞቴ ሆነ። ከኋላ በኩል ዓይንና ጀርባችንን መቧጠጫ ሶስተኛ እጅ ቢኖረን የሚለው ምኞቴ በከንቱነት ዘላለማትን ጠብቷል። በጽሞና ሰንብቶ ቀጠሮዬ ከእሷ ጋር የሆነ እለት ያቁነጠንጠኛል። ጀርባ ሲበላና አይነምድር ሲመጣ ስሜቱ አንድ አይነት ነው። ያቁነጠንጣል፣ መግቢያ ያሳጣል፣ የምንይዘው የምንጨብጠው እስኪጠፋን፡፡

እከክ መንፈሴ እንደሚለው በሕይወት ለም መሬት ላይ ያበቀልነው የሃጢያት ዛር ውላጇ የፈጠረው ይሆን? ነው ወይስ ተፈጥሮ ራሷ ብጉራም ሆና ከተፈጠርንበት አፈር የጸነሰችው? የቱም ይሁን ግድ የለኝም..ብቻ ጀርባዬ ላይ ፊጥጥ ከሚል እከክ የሚታደገኝ ባገኝ ለቱም ግድ አይኖረኝ።

ተፈጥሮ ለም መሬት ናት ብንል..እረ አይደለችም.. አራሙቻ አብቃይ መሬት ናት ብንል ወደልኩ የምንጠጋው ምን ይዘን ነው? ሁሉም የመሰለውን የሚሰነዝርባት ነጻ ዓለም ላይ ነን.. እንደዚህ መሆኑ ደግሞ ያላስታራቂ በየፊናችን እንድንቆም አድርጎናል። እንዲህ ጎራ የለየ ውንብድና ካልታከለበት መኖር ብቻውን አይጣፍጥ ይሆን?

ተናጋሪው መንፈሴ እንደሚለው የሕይወት ለምጽ የኩነኔ እፍታ ይሆን? ነው መሰል..ካልሆነ እንደሂሳብ ሊቅ አስልቶና ቀምሮ ጥሩ ጊዜዬ ላይ ለምን ይመጣል? ለዛውም እሷ ፊት ስቆም..ለዛውም እንከን በማይፈልግ ከፍታ ላይ፡፡

የሆነ ቦታ አለ..ተፈጥሮ ከሰውነት ስሪቷ የተረፋትን ጭቃና ብናኝ ያጎረችበት ጉሬ..ይሄ ቦታ ጀርባ ይመስለኛል። ካልሆነ እንዳይታይ ተከልሎን በፊትና ኋላ ለምን ቆምን? የሆነ ቦታ አለ ተንጠራርተንና ወደዚያ ወደዚህ ተንፈራግጠን የማንደርስበት ከሰውነት የራቀ ቦታ..ይሄን ሥፍራ የጀርባ ላይ ደሴት እለዋለው። እከክ ያቆረ..የሕይወት ቤርሙዳ። ልጅነቴ ጀምሮ ያበቃው ለአያቴ የጀርባ ማከኪያ ጉልጥምት እያቀበልኩ እንደሆነ የማልዘነጋው ትውስታ አለኝ። አያቴ ለምን ጀርባ ማከኪያ መቁያና ማማሳያ አቀብለኝ እንደምትለኝ አሁን ነው የገባኝ። መቼም በራስ ካልደረሰ አናውቅ..። ቆይ ግን በልጅነቴ ጀርባ አልነበረኝም..? ለአያቴ ጀርባ ማከኪያ ሳመላልስ በልቶኝ የማያውቀው! ነው ወይስ ከምናምንቴ ጋር እየታከኩ እከኬን አስታግሼው ይሆን?

ግራና ቀኝ እጄን በጎን ብልከው፣ በማጅራቴ በላይ ብሰቅለው፣ በታች በመቀመጫዬ በኩል ብሰደው ጀርባዬን አልደርስ አልኩበት። የበላኝን ቦታ አላገኝ አልኩት። ጀርባዬ አጠገቤ ቢሆን በጥፊ አላጋው ነበር። ሰከኘ እና አደብ ገዝቼ በምወዳት ሴት ፊት እንዳልታይ ያደረገኝ ባላንጣዬ፡፡

እሷ ፊት መጽዳት ነበር ፍላጎቴ..የበቃ መሆን። ግን ነጻ አልሆንም፣ ከጀርባዬ ጀምሮ አጓጉል ቦታ ላይ ያሳክከኛል። ብብቴ ውስጥ፣ መራቢያ አካላቴ ስር..እርምጥምጥ ቦታ ላይ። የሰላ ነገር ላይ እንዳረፈ መቀመጫ እንዲችው ስቁነጠነጥ እቆያለው። ልብሴ ተባይ አለው እንዳልል የጸዳ ነው ለበስኩት፡፡

አርፉ መቀመጧ ያስቀናኛል። ወለሉ ላይ የተሰተረው ጥላዋ እንኳን ዝማሜ የለውም። በስክነቷ ተፈጥሮን በሃይሏ የምትገዛ ትመስላለች። በርጋታዋ በጸጥታዋ ለተፈጥሮ ሥልጣኔን የምታስተምር ነው የምትመስለው። እዚች ሴት ፊት እከካም መሆን ምን እንደሚመስል ሳሉት፡፡

እንደእሷ ነበርኩ..እንደእሷም መሆን እፈልጋለው።

# ዓለም አቀፍ

## የሩሲያን የኒዩክሌር መሣሪያ አጠቃቀም የሚወስነው ሕግ እየተሻሻለ ነው - ፑቲን

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ በምዕራባውያን ኮንቬንሽናል ሚሳኤሎች ጥቃት ከደረሰባት የኒዩክሌር መሣሪያዎቿን ለመጠቀም እንደምትገደድ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን አስታወቁ።

ሞስኮ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ የኒዩክሌር መሣሪያዎቿን መቼና እንዴት መጠቀም እንዳለባት የሚወስነውን ሕጓን በማሻሻል ላይ መሆኗንም ነው ፕሬዚዳንቱ ያነሱት።

ፑቲን የሀገሪቱ የደህንነት ምክር ቤት ስብሰባን ሲከፍቱ የኒዩክሌር ሕጉን ማሻሻል ያስፈለገው ሞስኮ ለተደቀነባት አደጋ ምላሽ ለመስጠት ነው ብለዋል።

ማሻሻያው ኒዩክሌር ያልታጠቁ ሀገራት ከታጠቁት ጋር በመተባበር በሩሲያ ላይ ጥቃት ካደረሱ በሞስኮ ላይ "የጋራ ጥቃት" እንደከፈቱ ይቆጠራል የሚል ሃሳብ ማካተቱንም ተናግረዋል።

ሩሲያ የኒዩክሌር መሣሪያዎቿን መቼ መጠቀም እንዳለባት በግልጽ መስፈሩን በማንሳትም ከፍተኛ ድንበር አቋራጭ የሚሳኤል፣ የአየር እና ድሮን ጥቃት ከተፈጸመ ሀገራቸው አውዳሚዎቹን መሣሪያዎች መጠቀም እንደምትጀምር አብራርተዋል።

ሞስኮ አጋሯ ቤላሩስ ከተወረረች እና በኮንቬንሽናል መሣሪያዎች ጥቃት ከደረሰባት የኒዩክሌር መሣሪያዎቿን ልትጠቀም እንደምትችል መናገራቸውን ሬውተርስ ዘግቧል።

ሩሲያ በ2020 በይፋ ያወጣችውን የኒዩክሌር ሕግ እያሻሻለች መሆኑን ያስታወቀችው አሜሪካ እና ብሪታኒያ ለዩክሬን የላኳቸው ረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤሎች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ለማሳሰብ ነው ተብሏል።

በአሜሪካ የሚገኙት የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮልድሚር ዜለንስኪ ረጅም ርቀት የሚጓዙትን ሚሳኤሎች በመጠቀም ሩሲያን እንድትመታ ፈቃድ እንዲሰጧቸው ከፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ጋር ይነጋገራሉ ተብሏል።

ኬቭ ከዋሽንግተንም ሆነ ለንደን ፈቃድ ካገኘችና ሚሳኤሎችን ወደ ሞስኮ መተኮስ ከጀመረች ሶስተኛውና የኒዩክሌር ጦርነት



ሊጀመር ይችላል የሚሉ ተንታኞች፥ የኬቭ አጋሮች ይህን አደገኛ ውሳኔ ያሳልፋሉ ተብሎ እንደማይጠበቅ ይናገራሉ።

የዩክሬን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ አንድሪ ያምራክ ግን "ሩሲያ ዓለምን በኒዩክሌር ከማስፈራራት ውጭ አማራጭ የላትም" ሲሉ ለፑቲን ዛቻ ምላሽ ሰጥተዋል።

ሩሲያ በኒዩክሌር ጦር መሣሪያ አቅም የዓለማችን ቀዳሚዋ ሀገር ናት። በዓለም ላይ ከተመረቱ የኒዩክሌር አረሮች 88 በመቶው በሩሲያ እና አሜሪካ ነው የሚገኙት።

"ኒዩክሌር የዜጎቻችን ደህንነት ለማስጠበቅም ሆነ የዓለም ሥርዓት ሚዛንን ለማስተካከል ዋነኛው አማራጭ ነው" ያሉት ፕሬዚዳንት ፑቲን፥ ምዕራባውያን ሀገራት "በእሳት እንዳይጫወቱ" አሳስበዋል ተብሏል።

## አሜሪካና አጋሮቿ በሄዝቦላህና እስራኤል መካከል ለ21 ቀናት የተኩስ አቁም እንዲደረግ ጠየቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካ እና አጋሮቿ በሊባኖስ እና እስራኤል መካከል የ21 ቀናት የተኩስ አቁም እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

ከዚህ ባለፈም ሁለቱ አካላት ግጭቱን ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ መፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አስተዳደር እንደሚያመቻች ተገልጿል።

ሀገራቱ ከሊባኖስ በተጨማሪ የጋዛው ጦርነት ላይ ተኩስ አቁም ተግባራዊ እንዲደረግ እና ወደ ግጭት ማቆም ምክክሮች እንዲገባ ነው ጥሪ ያቀረቡት።

ከ79ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ጎን ለጎን ባደረጉት ውይይት የተኩስ አቁም እንዲደረግ የጠየቁት ሀገራት አረብ ኤሜሬትስ፣ አውስትራሊያ፣ ሳኡዲአረቢያ፣ የአውሮፓ ህብረት እና አሜሪካ ናቸው፡፡

በነጩ ቤተ መንግሥት ይፋ በተደረገው የሀገራቱ የጋራ አቋም መግለጫ ላይ በቀጣናው እያደገ የመጣው ሁሉን አቀፍ ጦርነት በአካባቢ ተጨማሪ የደህንነት ስጋት ማንገሡን ገልጾ በውጥረት ውስጥ የሚገኙ አካላት ከዚህ ድርጊት እንዲታቀቡ ጠይቋል፡፡

ካለፈው ሰኞ ጀምሮ በሊባኖስ መጠኑ ከፍ ያለ የአየር ጥቃት እየፈጸመች የምትገኘው እስራኤል ከትናንት በስቲያም አጠናክራ በቀጠለችው ጥቃት 72 ሰዎች ሲገደሉ 223 ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸውን ሮይተርስ የሊባኖስ የጤና ሚኒስቴርን ጠቅሶ ዘግቧል፡፡

የእስራኤል ወታደራዊ አዛዥ በሊባኖስ የምድር ላይ ጥቃት ሊከፈት እንደሚችል ተናግረዋል። ይህም ሲፈራ የነበረውን ሁሉን አቀፍ ጦርነት የሚያስከትል ውሳኔ ሊሆን ስለሚችል ይህ ከመሆኑ በፊት ውጥረቱን ለማርገብ ነው አሜሪካ እና አጋሮቿ የተኩስ አቁም ጥሪውን ያቀረቡት፡፡

በመንግሥታቱ ድርጅት የእስራኤል አምባሳደር ዳኒ ዳኖን ሀገራቸው ዲፕሎማሲያዊ አማራጮችን ለመመለከት ፈቃደኛ እንደሆነች ተናግረው በቀጣናው ሰላማዊ ድርድር እንዳይሳካ የምታበላሸው "የአካባቢው በጥባጭ" ኢራን ነች ሲሉ ከሰዋል፡፡

የኢራኑ አምባሳደር አባስ ርካቺ በበኩላቸው ኢራን በቀጣናው የሚገኘው ውጥረት ከዚህ የበለጠ እንዲሰፋ ባትፈልግም በሄዝቦላ እና እእራኤል መካከል ጦርነት ከተጀመረ ግን ቴሄራን ሄዝቦላህን እንደምትደግፍ አስረግጠው ተናግረዋል።

አሜሪካ እና አራት አጋሮቿ ያቀረቡትን የሊባኖስ ተኩስ አቁም ስምምነት ጥሪ ከመሪዎቹ ጋር እንደሚመክሩበት ይጠበቃሉ፡፡

ቴልአቪቭ ከሰኞ አንስቶ በሊባኖስ የተለያዩ አካባቢዎች እየፈጸመችው በምትገኘው የአየር ጥቃት እስካሁን ከ550 በላይ ሰዎች ሲገደሉ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች ደግሞ ተፈናቅለው በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ይገኛሉ፡፡



ማህበራዊ

**ሀገርኛ**

# መስቀል- በሶዶ ክስታኔ ቤተ-ጉራጌ

**ማህሌት አብዱል**

ወርሃ መስከረም መስኩ በልምላሜ በአደይ አበባ የምታሸበርቅበት፣ ወንዙ ጅረቱ የሚጠራበት፣ ዝናብና ጉሙ አልፎ፣ ጭቃው ጠፎ፣ ነፋሻ አየር የሚነፍስበትና ጸሀይ የምትደምቅበት ወቅት ነው። የክረምቱ ወቅት የሚወጣበትና የበጋው ወቅት መግባት የሚጀምርበት፣ አዝመራው የሚያብብበት፣ ስሜት በደስታ የሚሞላበት እንደመሆኑም በልዩ ሁኔታ ይታያል፡፡

በዚህ ወቅት በርካታ ሃይማኖታዊ ባህላዊ ይዘት ያላቸው በዓላት የሚከናወኑበት መሆኑ ብዙዎች ወሩን የደስታና የፌሽታ አድርገው ያስቡታል፤ በናፍቆት የሚጠብቁትም ነው። በድምቀት ከሚከበሩ ሃይማኖታዊ በዓላት አንዱ ደግሞ የመስቀል በዓል ነው። በእርግጥ! መስቀል የአካባበሩ ሁኔታ ይለያይ እንጂ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እንደየባህላቸው፤ ታሪካቸውና ቋንቋቸው በተለየ መንገድ ያከብሩታል። በርካታ ባህላዊ እሴት ያላቸው ክዋኔዎች ያሉበት መሆኑ ደግሞ የተለየ ያደርገዋል፡፡

መስቀል በድምቀትና በበርካታ ክዋኔዎች ከሚያከበሩ የሃገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል የጉራጌ ብሄረሰብ አንዱ ነው። መስቀል በሁሉም ቤተ-ጉራጌ ብሄረሰብ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው፤ ከሃይማታዊ ይዘቱ በተጨማሪ ባህላዊና ማህበራዊ መስተጋብሩ የላቀ በመሆኑ ተወላጆቹን ብቻ ሳይሆን የሌላ አካባቢ ነዋሪዎችም ጭምር ቦታው ድረስ ሄደው እንዲያከብሩት የሚያጓጓና የሚያስናፍቅ በዓል ነው። እኛም በዛሬው ሃገርኛ አምዳችን የሶዶ ክስታኔ (ሶዶ ጉራጌን) የመስቀል በአል አካባበርና ባህላዊ ኩዋኔዎችን እናስቃኛችኋለን፡፡

የመስቀል በዓል አጀማመር የእየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል ከማግኘት ጋር ተያይዞ የተጀመረ ሲሆን እያንዳንዱ የክርስትና እምነት ተከታይ/ በተለይ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች/ በዓሉን የሚያከብሩት እንደ ሕዝቡ ባሕል አኗኗርና ወግ በመሆኑ ከሃይማኖታዊ ስርዓት ባሻገር ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ፋይዳው የጎላ ስለመሆኑ ይገለጻል። የመስቀል በዓል የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተራራቁ የሚቀራረቡበት፣ ወጣቶች የሚተጫጨበት፣ ጋብቻ የሚመሰርቱበት፣ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖረው የብሄረሰቡ አባል ያለውን ይዞ ወደ ትውልድ ቀየው በመሄድ ለአባት ለእናቱ ለጎረቤቱ በመስጠት የሚመረቅበት፣ ለመጪው ዓመት የሚታቀድበት፣ በሰላም ላደረሳቸውና ለፈጣሪያቸው ምስጋና፤ ለወዳጆቻቸው ምኞታቸውን የሚገልጹበት በዓል ነው።

ወይዘሮ ማሜ ጌታቸው የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልሉ የምስራቅ ጉራጌ ዞን የቡኢ ከተማ አስተዳደር ባሕልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ በሶዶ ክስታኔ ማሕበረሰብ መስቀል በዓመት ከሚከበሩ አንዱና ትልቁ በዓል ነው። መስቀል ከሌሎች ሃይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላት ለየት የሚያደርገው በዋናነት የተራራቁ ቤተሰቦችን የሚያቀራርብ፤ የተጣሉ የሚታረቁበትና የተለያዩ ክዋኔዎች የሚከናወኑበት መሆኑ ነው። መስቀል ለክስታኔ ሕዝብ ዓመቱን ሙሉ በተለያዩ ዝግጅቶች በጉጉት የሚጠበቅ ሲሆን፣ በተለይ ከነሐሴ ወር ጀምሮ ደመራ በማዘጋጀትና የተለያዩ ለበዓሉ ድምቀት የሚውሉ ስራዎችን የሚሰሩበት መሆኑ የተለየ ያደርገዋል።

የክስታኔ ሕዝብ ዓመቱን ሙሉ በጉጉት ሲጠብቀውና ሲዘጋጅበት የሚቆይበት ይሁን እንጂ በተለይም ከመስከረም 12 እስከ ጥቅምት 5 ድረስ በተለያዩ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ባላቸው ክዋኔዎች በድምቀት የሚከበር መሆኑን ያነሳሉ። ‹‹የሶዶ ክስታኔ ቤተ-ጉራጌ የመስቀል በዓልን የበዓሎች ሁሉ አውራ አድርጎ ሲያከብር ኖሯል፤ ለእዚህ አከባበርም አስቀድሞ ሰፊ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፤ በዓሉን ከመስከረም 12 እስከ ጥቅምት አምስት ድረስ እየጨፈረና ለበዓሉ ተብሎ የተዘጋጁ ምግብ አይነቶችን እየተመገበ ያከብራል›› ሲሉም ይገልጻሉ። በእያንዳንዱ ቀን ስለሚከናወነው ተግባርም ኃላፊዋ አብራርተዋል፡፡

**መስከረም 12 ቀን ‹‹ሴማት ያወርድቦማይ››**

እንደ ወይዘሮ ማሜ ማብራሪያ፤ መስከረም 12 በሶዶ ክስታኔ ማሕበረሰብ የመስቀል በዓል ለምግብ ማቅረቢያነት የሚውሉ ቁሳቁስ ከተሰቀሉበት ስፍራ የሚወርዱበት ቀን ነው። በዚህ እለት ከማጀት እስከ ደጅ ድረስ የፅዳት ስራ ይካሄዳል፤ ግድግዳ በተለያዩ ቀለማት እንዲደምቅ ይደረጋል።

መስከረም 12 በሶዶ ክስታኔ ማሕበረሰብ ‹‹ሴማት ያወርድቦማይ›› ይባላል። በዚህ እለት የተለየዩ የቤት እቃዎች ጽዳት የሚደረግበት ቀን ነው። በእዚህ ቀን ቁሳቁስ



በጥንቃቄ ታጥበውና ፀድተው እስከ ጥቅምት 5 ድረስ ለምግብ ማቅረቢያነት አገልግሎት እንዲውሉ ይደረጋሉ።

**መስከረም 13 - ‹‹ዎልቀነ››**

መላው ክስታኔ በእዚህ ወር ‹‹ማኛም በኬር አሰላንህም፤ አሰላነ›› እያለ የእንኳን አደረሰን መልእክት ይለዋወጣል፤ መስከረም 13 ቀን ግን ሴቶች በተለየ መልኩ የሚከበሩበት እለትና የተለየ ክዋኔ የሚደረግበት ነው። ይህ ቀን በሶዶ ክስታኔ ማሕበረሰብ ‹‹ዎልቀነ›› ተብሎ ይጠራል፤ በዚህ እለት ጎመን ከማሳ ካለ የሚለቀምበት፤ ከሌለ ደግሞ ከገበያ ተገዝቶ በትልቅ እንስራ ተቀቅሎ፤ ልክ እንደ ክትፎ ሁሉ ደቆ ተክትፎና በቂቤ፤ በኮረሪማና በሌሎችም ቅመማቅመሞች ታሽቶና ተዋዝቶ ይዘጋጃል።

የመስቀል በዓል ዝግጅቶች የሚያጠናቅቁበት እለትም ነው። ለመስቀል ተብለው በተዘጋጁት በሁሉም የምግብ ዓይነቶች ላይ የሙከራ ቅምሻ የሚደረግበት (የሚበላበት) እና የጎመን ቀን እየተባለ በተለምዶ የተሰየመ እለት ነው። በተጨማሪም በዕለቱ ‹‹ኸቆት›› አይብ መጠኑ ከጎመን የሚያንስበት አይነት ምግብ ተዘጋጅቶ የሚበላበትና ሴቶች በሚገባ እንዲመገቡ የሚደረግበት ነው።

ወይዘሮ ማሜ እንደሚሉትም፤ እንደ ዓለም የሴቶች ቀን (ማርች ኤይት) ሁሉ ሴቶች በዚህ ቀን ጎልተው ይታያሉ፤ ይደምቃሉ፤ ይደመጣሉ፤ የፈለጉትን ሁሉ እንደልባቸው ያከናውና። በዚህ ቀን ሴቷ ምንም አይነት ጥፋት ብትሰራ ማንም ቀና ብሎ እንደማያያት እንደማይናገራት ኃላፊዋ አስገንዝበዋል።

**‹‹ዎልቀነ ዎልቀነ**

**ምሽት ይገራቦ ቀነ**

**ታምብል ይጋም ኮነ**..›› እየተባለ በዚህ ቀን ሴቶች በተለየ መልኩ ስማቸው እየተነሳ ይጨፈራል።

ኃላፊዋ የዚህን ባሕላዊ ዜማ ትርጓሜ ሲያስረዱ ‹‹በዕለቱ ምንም መበያ የሚሆናት ነገር ብታጣ ብታጣ የጎመን ውሃ አታጣም ማለት ነው›› ይላሉ። በእዚህ እለት ማንኛውም የሶዶ ክስታኔ ሴት እሷም ከሰራችውና ቤት ካፈራው የምትበላበትና የምትጠግብበት በደስታ የምታከብርበት ቀን ነው። ይህም በመሆኑ እለቱ ‘የሴቶች ቀን’ ወይም ‹‹ዎልቀነ›› እየተባለ እንደሚጠራ ያመለክታሉ። የአካባቢው ተወላጆችም ለመመረቅ እጃቸውን ያፈራውን ለእናት አባቶቻቸው እና ለጎረቤትም ጭምር ይዘው እንደሚሄዱም ተናግረዋል።

**መስከረም 14 ቀን ‹‹ደንጌሳት››**

በሶዶ ክስታኔ መስቀል በድምቀት ከሚከበርባቸው ቀናት አንዱ መስከረም 14 ቀን ይጠቀሳል። ይህ እለት በማሕበረሰቡ ዘንድ ‹‹ደንጌሳት›› በመባል ይጠራል፤ ትርጉሙም ደስታ ወይም ፍሰሀ ማለት ነው። በዚህ ቀን ማምሻ ያላገቡ ወጣቶችና ዕድሜያቸው ከዚያ በታች ያሉ የልጆች ደመራ የሚያቃጥሉበት ሲሆን፣ በማሕበረሰቡ አጠራር የልጆች እሳት ወይም ዳመራ ‹‹የባዮች ኸሳት›› ይባላል።

በእለቱ ለሁሉም የቤተሰብ አባል የተዘጋጀለትን ‹‹ደንጋሳ›› የጎመን ክትፎ እና አይብ የሚበላበት፤ በተለይ እናት ለልጆች እንደየድርሻቸው ጎመን በአይብ የምትሰጥበት ቀን ነው። ቀኑ የሴቶች ድርሻ ጎልቶ የሚታይበት በመሆኑ እናቶችም ሙሉ ዝግጅት ማድረጋቸውንና የቤት አባወራ እንዲገኝላቸው ብቻ ለማመላከት ለማሕረሰቡ በስንኝ ቋጠሮ ይገጥሙታል።

**‹‹በርበሬም ዎቀጥኩም**

**ጥወም አቅሳስጥኩም**

**አምበልም አረጥኩም**

**ጉንስም አልባበጥኩም**

አናቀርብሆኖ የጌ አቢ ቀበጥኩም...›› እየተባለ የሚዜምበትና የሚጨፈርበት ቀን መሆኑን ወይዘሮ ማሜ ይናገራሉ። ይህም በርበሬ መወቀጡን፤ ቂቤ መነጠሩን፤ ጎመኑም መከተፉን፤ ቆጮም መጋገሩን እንዲሁም ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ሁሉ ስንዱ መሆናቸውንና ለማቅረብ አባወራ እንደሚጠብቁ ለማንፀባረቅ የሚዜም ማራኪ ዜማ ነው።

በአንፃሩ ደግሞ በቂ ዝግጅት ያላደረገች እመቤት ‹‹የደንጌሳቲማይ ቃዪሲ ባያንሴ

አዮዲ ትሙትም ሀዘንኪ የባሴ›› በሚል የስንኝ ቋጠሮ የምትችበት ሁኔታ እንዳለም ገልጸዋል፤ ይህንንም ትችት በመፍራት ሁሉም የክስታኔ ሴቶች አስቀድመው ዝግጅታቸውን ለማጠናቀቅ እንደሚታትሩም ያመለክታሉ።

**መስከረም 15 ቀን ‹‹የእርድማይ››**

መስከረም 15 በሶዶ ክስታኔ ቤተ ጉራጌ ጨርቆስ ወይም ‹‹የእርድማይ›› ተብሎ ይጠራል፤ በዚህ ቀን የአባወራዎች ተግባር ጎልቶ ይታያል። ስለሆነም አስፈላጊውን ዝግጅት ለአንድ ዓመት ሙሉ ቆጥበው በሬ ገዝተው የሚያርዱበት ቀን መሆኑን ወይዘሮ ማሜ ያስረዳሉ። ሆኖም በዚህ ቀን አባወራው ያረደው ሰንጋ የደለበ ካልሆነ ሴቶች በግጥም ይተቹታል።

**‹‹ጩሮደም ኸጭንን**

**ቅብዲም ነስጭን**

**የመናጊ ጠብጠት ንቶናም በጨበር**

ደናኛ ንኸ'ንን...›› በማለት ይወርፉታል። ይህም ማለት ‹‹ስጋውንም ብላው፤ ቂቤውዬንም ልጠጣው፤ በማግስቱ ጠዋት ፀሀይ ላይ ቁጭ ብለን መልካችን እንየው›› በማለት የተሻለው የማነው በማለት ዝግጅቱ በቂ ያለመሆኑን የሚያስረዱበት ሁኔታ መኖሩን ይጠቅሳሉ፡፡

**በተጨማሪም ‹‹በሰርደ የጣየ**

**ጂስል በገባየ**

**ምን ነይዝም ነውጣየ**

አዚ የደነገጥኩን በደኸ የግባየ›› በማለት ባሎቻቸውን በዜማው የሚወርፉ መሆናቸውን ኃላፊዋ ይገልፃሉ። ይህም ማለት ‹‹ስጋው የበግ ኩሽና ብገባም ይገኔ የምወጣው ስላጣው ደነገጥኩኝ፤ ድንጋጤዬ የአንተ ይሁን›› የሚል ይዘት ያለው መሆኑን ያስረዳሉ።

በአንፃሩ ደግሞ የአባወራው የተሻለ ሆኖ የእማወራ ካነሰ ‹‹ቅብደሽ የሀምሌ ነሀሴ

ልብለበው የባሴ›› በሚል የአሹሙር ይዘት ባለው ቅኔ ይወርፏታል። ይህም ማለት ቅቤሽ ለጋ ስለሆነ ቃር አስቸግሮኛል የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑን ያባራራሉ።

በሌላ በኩል ግን በዚህ እለት ስጋ ያልገባላት ከሆነች በማህበረሰቡ ዘንድ የተፈታች ተደርጎ ታሳቢ ይደረጋል። ባል የሞተባት ከሆነች ደግሞ ዘመድ አዝማዱ ተሰባስቦ ስጋ ያስገባላታል፤ ምክንያቱም ባሏን አስባ እንዳታዝን በማሰብ እንደሆነ ይናገራሉ። ‹‹ባል የሞተባት ሚስት እስከ አንድ ዓመት ስጋ ሳትበላ የምትቆይበት ስርአት ጎጂ ልማድ በመሆኑ ከ 40 ቀን በምንም መልኩ መብለጥ እንደሌለበት የሶዶ ጎርደና ሴራ ያስቀምጣል›› ሲሉም ያክላሉ።

**መስከረም 16 ቀን ‹‹የኸሳትማይ››**

በማሕብረሰቡ መስከረም 16 ቀን ‹‹የኸሳትማይ›› በመባል ይጠራል፤ ቀኑ ዋናው ዳመራ የሚበራበት ነው። ከነሐሴ 12 ጀምሮ የተደመረውን ዳመራ በዚህ እለት የአካባቢው ማሕበረሰብ ተሰባስቦ ያበራል። በአብዛኛው ሃይማኖታዊ ክዋኔ የሚደረግበት ቀን ሲሆን፣ ከቤተ-ክርስቲያን መልስ ሁሉም በየአካባቢው የተዘጋጀ ደመራ በማቃጠል ክትፎ በቆጮ (ብርንዶ በአልበበጫት) ቀርቦ የሚበላበት፤ የሚጨፈርበት ቀን መሆኑንም ያመለክታሉ።

በዚሁ ወቅትም አባቶች ልጆችንም ሆነ መላው የአካባቢውን ሕዝብ የሚመርቁበት ስርዓትም እንደሚከናወን ይጠቅሳሉ። ከባሕላዊ ክዋኔዎች ጎን ለጎን ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ስርዓቶች እንደሚካሄዱ አስታውሰዋል። በዚህ እለትም ጎልቶ ከሚታወቁትና በስፋት ከሚዜሙት የቀየው ባሕላዊ ዘፈኖች መካከል ‹‹ብርንዶ በወጨት ይቄኖት

**ቅብም ይስግቦት**

**አልበበጫት ይፈርሙም**

**በሴማት ያቀርቡም**

**ዚሆም ይደንቅቦትን**

**ነግዳ ይቂበልቦትን**

**የማንም ተሻልሙ**

**ክስታኔ ዝወርሙ**

**ስም ይነንትን ሶዶ**

ድሮም በብርንዶ...›› በማለት በእለቱ ክትፎ የመብላት ሂደትንና የአቀራረብ ስርዓቱን የሚያሳዩ ዘፈኖች እየተዘፈኑ ፤ በጭፍራ ሌቱ የሚነጋበት ሁኔታ እንዳለም ነው ያመለከቱት።

**መስከረም 17 ቀን መስቀል**

ይህ ቀን ልክ በተለይ የግማደ መስቀሉ መገኘትን ምክንያት በማድረግ በልዩ ሁኔታ የሚከበርበት ሲሆን፣ በዚህ እለትም የብሔረሰቡ መታወቂያ የሆነውን ክትፎን ጨምሮ ቁርጥና ሌሎች ባሕላዊ ምግቦች በስፋት ይበላሉ። ከዚሁ በተጓዳኝ የተነፋፈቀ ዘመድ አዝማድ ይወያያል፤ ይመራረቃል፤ ይጠያየቃል።

**አዳብና**

አዳብና በሶዶ ክስታኔ ማሕበረሰብ መስቀልን ተገን አድርገው ከሚከናወኑ ባሕላዊ ክዋኔዎች ዋነኛው ነው። ይህም ወጣት ወንዶችና ሴቶች በተለይ ገበያ ባለባቸው ቦታዎች ላይ የሚያካሂዷቸው ባሕላዊ ጫወታዎች እና ጭፈራዎች የሚከናወንበት ስርዓት መሆኑን ያስረዳሉ። ይህም ባሕላዊ ክዋኔ ከመስከረም 16 የሚጀምር ሲሆን፣ እስከ ጥቅምት አምስት ድረስ ገበያ ባለባቸው ቦታዎች ይቀጥላል። ወንዱ የሚፈልጋትን የሚመርጥበትና የሚያጭበት ወቅትም መሆኑን ጠቅሰው፤ ሌላውን የሰርግ ስርዓት ደግሞ ቤተሰብ የሚጨርስበት ሁኔታ መኖሩን ያብራራሉ፡፡

መስቀል ለክስታኔ ቤተ ጉራጌ የሁሉም ነገር መገለጫ መሆኑን ኃላፊዋ ጠቅሰው፤ በተለይም በመላ ሃገሪቱ የሚኖረው ይህ ማሕበረሰብ ዓመቱን ሙሉ ለፍቶ ያገኘውን ከቤተሰቡ ጋር የሚቋደስበት፤ ስጦታ የሚለዋወጥበት፤ የሚተጫጭበት መሆኑ የተለየ እንደሚያደርገው ይገልፃሉ።

የትኛውም የብሔረሰቡ ተወላጅ በዚህ ወቅት ትውልድ አካባቢው የመግባት ግዴታ እንዳለበት መሆኑን ይናገራሉ። ገንዘብ ባይኖረውም እንኳን የወላጆቹን እርግማን በመፈራትና ከእነሱ የሚያገኘውን ምርቃት ታሳቢ በማድረግ በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ለመስቀል ሃገሩ የሚገባበት ሁኔታ መኖሩን ያመለክታሉ። ይህም የጉራጌ ማሕበረሰብ ለወላጆችና ሆነ ለምርቃት ያለውን ከፍ ያለ ስፍራ እንደሚያሳይ ይናገራሉ፡፡

‹‹ማሕበረሰቡ በተለይ ለታላላቆችና ለአባቶች ትልቅ ክብር ይሰጣል፤ በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን እነሱን ተሻግሮ የሚሄድ አንድም ሰው የለም›› የሚሉት ወይዘሮ ማሜ፤ ይህ የመከባበርና የመቻቻል መሰረቱ ቤተሰብ መሆኑን እንደሚያመላክት ያስረዳሉ። ‹‹ ይህም እየተመናመነ የመጣው የመከባበርና የመቻቻል እሴት እንዲያንሰራራ ጥሩ ተምሳሌት ይሆናል›› ይላሉ። እንዲህ አይነቱን የመደማመጥና የመከባበር እሴት በማዳበር ሁሉም ለዘላቂ የሃገር ሰላም የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

# የመስቀል ደመራ

## በዓል ታሪካዊ አመጣጥና አከባበሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኢትዮጵያ በድምቀት እና በሽር ጉድ ከሚከበሩት በዓላት መካከል አንዱ መስቀል ነው። የመስቀል በዓል በወርሃ መስከረም በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በተለይም ደግሞ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዕምነት ተከታዮች በድምቀት የሚከበር ትልቅ በዓል ነው። በአብዛኞቹ የሕዝበ ክርስትና ተከታዮች ዘንድ እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መሣሪያ መስቀል ተብሎ እንደሚጠራ ይነገራል፡፡

"cross (ክሮስ)" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተወሰደው ‹‹ክሩክስ›› ከሚለው የላቲን ቃል ነው። ሆኖም የመስቀል አምልኮ ከክርስቶስ ዘመን በፊትም ጀምሮ የነበረ ለመሆኑ በርካታ የጽሑፍና የሥነቁፋሮ ማስረጃዎች ያስረዳሉ። ከክርስትና ዘመን በፊት ጀምሮ በሁሉም የጥንቱ ዓለም ክፍሎች የተለያየ የመስቀል ቅርጽ ያለባቸው የተለያዩ ዕቃዎች መገኘታቸው ይነገራል። ለአብነት በሕንድ፣ በሶሪያ፣ በፋርስና በግብፅ ቁጥር ስፍር የሌላቸው መስቀሎች ተገኝተዋል። ከክርስትና በፊት በነበሩት ጊዜያትና ክርስቲያን ባልሆኑት ሕዝቦች መካከል መስቀልን እንደ አንድ ኃይማኖታዊ ምልክት አድርጎ መጠቀም በመላው ዓለም ላይ የተለመደ ልማድ እንደነበር የተለያዩ ድርሳናት ይጠቅሳሉ።

ቅዱሳን መጽሃፍት እንደሚያትቱት መስቀል ማለት "ሰቀለ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን መስቀያ ወይም መከራ ማለት ነው። መከራም የተባለበት የጥንት ሮማውያን ወንጀለኛን በሞት የሚቀጡት በመቀልያ እንጨት ላይ እየሰቀሉ ስለነበር ነው። አይሁድም ከገዥዎቻቸው በወረሱት ልማድ መሠረት ያለምንም ሀጥያት እና በደል አጥፊ ነው ብለው የፈረዱበትን እየሱስ ክርስቶስን ከወንበዴዎች ጋር በዕፀ መስቀል ሰቅለው በሞት ቀጡት፡፡

ይህ መድህኒተ ዓለም የተሰቀለበት መስቀልም እንደማይጠቅም ሰባራ እቃ የትም ከተጣለ በኋላ እውራን፣ አንካሶች፣ለምጽ የያዛቸው፣ አጋንንት ያደረባቸው፣ ሰይጣን የለከፋቸው ሕሙማን ሁሉ እየሄዱ ሲዳስሱት ከየበሽታቸው ስለፈወሳቸው ይሁድ በክርስቶስ ገቢረ ታምር ይናደዱ እንደነበር ሁሉ የመስቀል ድውያንን መፈወስ ደግሞ ይበልጥ ስላበሳጫቸው ንዴታቸውን ለማብረድ ጉድጓድ ምሰው እንደቀበሩት ያስረዳል፡፡

የመስቀል በዓል ከዋዜማው ጀምሮ የሚከበር ሲሆን፤ የዋዜማው በዓል ደመራ በመባል የሚታወቅና በአደባባይ በድምቀት የሚከበር ነው። የመስቀል በዓል ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ብዙ ትርጉም ዓለው። በዓሉ እየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ነጻ ለማውጣት ወደ ምድር በመምጣት ተሰቅሎ ጨለማን ወደ ብርሃን የቀየረበት በመሆኑ የእምነቱ ሊቃውንት አስተምሮ ያስረዳሉ።

እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በአረማውያን ለረጅም ዘመናት ተደብቆ ቆይቶ ነበር። እስራኤላዊዋ ንግስት እሌኒ በእግዚያብሄር መሪነት ይህን መስቀል በ16 በጭስ እየተመራች እውነተኛውን መስቀል ያገኘችበት ዕለት ነው።

የቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚያስረዱት፤ መስቀሉ የተገኘበት ዕለት መስከረም 17 እንዲከበር በወሰኑት መሰረት በዓሉ ይከበራል። ምዕመናን በየዓመቱ መስከረም 16 ደመራን የሚያከብሩት የንግስት እሌኒ በጭስ ታግዛ መስቀሉን ያገኘችበትን ሁነት ለማሰብ ነው። እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ግማሹ በኢትዮጵያ ወሎ ውስጥ ግሸን ደብረ ከርቤ እንደሚገኝና ቀሪው የመስቀሉ ክፍል በተለያዩ ሀገራት እንደሚገኝ ያስረዳሉ። ይህ መስቀል ከተገኘ 5 ሺህ 500 ዓመታትን እንዳስቆጠረ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች የሚሉት ቀሲስ ታምራት፤ መስቀሉ በእስራኤል ውስጥ ጎለጎልታ ተብሎ በሚጠራው ተራራ ላይ መገኘቱን ይናገራሉ።

ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከወደቀበት መርገም ያድነው ዘንድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በ33 ዓመቱ በራሱ ፈቃድ በመስቀል ላይ ተሰቀለ። በመገረፉ ቁስል እኛ ተፈወስን (1ጴጥ 2፥24)። በስቅለቱም ዲያብሎስን ድል ነሥቶ በወህኒ /በሲዖል/ ለነበሩ ነፍሳት ነጻነትን ሰበከላቸው (1ጴጥ 3፥18-19)። የሰው ልጅ በሙሉ ከዲያብሎስ ባርነት ፍጹም ነጻ ወጣ። ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ሕዝብና አሕዛብን በአንድ አካል ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ (ኤፌ 2፥16)። ከፍተኛ ወንጀል የሠሩ ሰዎች ብቻ ይሰቀሉበት የነበረው መስቀል ከጌታ ስቅለት በኋላ የመዳን ምልክት መሆኑን ቅዱሳን መጽሃፍት ያስረዳሉ፡፡

ይሁን እንጂ ጌታ የተሰቀለበት መስቀል ተአምራትን በማድረጉ የታወኩ አይሁድ መስቀሉን ከሰዎች እይታ ለመሠወር ወስነው ጉድጓድ ቆፍረው ቀበሩት። መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ለ300 ዓመታት ያህል የቆሻሻ መጣያና ማከማቻም እንዳደረጉት ስለመስቀል በዓል የተጻፉ ታሪካዊና ኃይማኖታዊ መጽሃፍት ይዘክራሉ። ምንም እንኳን አይሁድ ለጊዜው መስቀሉን ከዐይን ለመሰወር ቢችሉም ከክርስቲያኖች ልቡና ግን ሊያወጡት አልቻሉም። የመስቀሉ ብርሃን በልቡናቸው የሚያበራ ክርስቲያኖች እየበዙ መጡና መስቀሉንም መፈለግ ጀመሩ። ይህ ሂደት በንግስት እሌኒ ጋር ያለው ትስስር ምን እንደሆነ በዝርዝር መመለከት ያስፈልጋል።

**የንግሥት እሌኒ ድካምና ፍሬ**

ንግሥት እሌኒ ልጇን ቆስጠንጢኖስን ከልጅነቱ ጀምሮ ስለ ክርስትና ሃይማኖትና ስለ ክርስቲያኖች መከራ ታስተምረው ስለነበር በክርስቲያኖች ላይ የነበረው አመለካከት በሮም ከነገሡት ቄሣሮች ሁሉ የተሻለ ነበር፡፡ ቆስጠንጢኖስ የሮም ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ በ300 ዓመታት ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ ለክርስቲያኖች የነጻነት ዐዋጅ ዐወጀ። ክርስትናም ብሔራዊ ኃይማኖት ሆነች። ንግሥት እሌኒም የተፈጠረውን አመች ሁኔታ በመጠቀም የጌታችንን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት በ327 ዓ.ም ወደ እየሩሳሌም እንደሄደች ስለመስቀል የተጻፉ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

ንግሥት እሌኒ ልጇ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነላት ወደ እየሩሳሌም ሔዳ መስቀሉን ለመፈለግ እንዲሁም በእየሩሳሌም ያሉ ቅዱሳት መካናትንና አብያተ ክርስቲያናትን ለማሳነፅ ለእግዚአብሔር ተሳለች። ከዚህ በኋላ ቆስጠንጢኖስ አምኖ በ337 ዓ.ም ተጠመቀ። ቅድስት እሌኒም ወደ እየሩሳሌም ሔደች እንደደረሰችም ስለ ክብረ መስቀል መረመረች ጠየቀች። ቦታውን የሚያስረዳት ግን አላገኘችም። አይሁድ የተቀበረበትን ቦታ ለማሳየት ባይፈልጉም በኋላ ባደረገችው ጥረት አረጋዊው ኪራኮስ የጎልጎታን ኮረብታ አመላከታት ዳሩ ግን ኪራኮስ ዘመኑ ከመርዘሙ ጋር ተያይዞ በአካባቢው ከነበሩት ከሦስቱ ተራሮች ውስጥ መስቀሉ የሚገኝበት የትኛው እንደሆነ ለይቶ ማወቅ አልቻለም፡፡

ንግሥት እሌኒ ከሦስቱ ተራሮች የቱ እንደሆነ ለመለየት በእግዚአብሔር መልአክ እርዳታ ደመራ አስደምራ ብዙ እጣንም በመጨመርና በማቃጠል ጸሎት ተያዘ። የእጣኑ ጢስ ወደ ሰማይ በመውጣት በቀጥታ ተመልሶ መስቀሉ ባለበት ተራራ ላይ በማረፍና በመስገድ መስቀሉ ያለበትን ትክክለኛ ስፍራ አመለከታት። ቅዱስ ያሬድም ጢሱ ሰገደ ብሎታል። ከዚያም መስከረም 16 ቀን ቁፋሮው እንዲጀመር አዘዘች። ሰባት ወር ያህል ከተቆፈረ በኋላ መጋቢት 10 ቀን ሦስት መስቀሎች በአንድነት ተገኙ። የክብር ባለቤት ጌታችን የተሰቀለበት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ተቸገሩ፡፡

መስቀሎቹን ወስደው በሞተ ሰው በተራ ቢያስቀምጡ ጌታችን የተሰቀለበትና በዕለተ ዐርብ ተሰቅሎ የዋለበትና በደሙ መፍሰስ የተቀደሰው መስቀል የሞተውን ሰው በማስነሣት በሠራው ተአምር ሌሎቹ ሁለቱ ታምራት ባለማድረጋቸው የጌታን መስቀል ለይቶ ማወቅ ተችሏል። እሌኒና ክርስቲያኖች ሁሉ ለመስቀሉ ሰገዱለት። በየሀገሩ ያሉ ክርስትያኖች ሁሉ የመስቀሉን መገኘት በሰሙ ጊዜ መብራት አብርተው ደስታቸውን በመግለጥ ለዓለም እንዲታወቅ አደረጉ። ንግሥት እሌኒ ለመስቀሉ ቤተ መቅደስ ከሠራችለት ጊዜ ጀምሮ በመስከረም 17 ቀን አሁን በኢትዮጵያ እንደሚከበረው በክርስቲያኖች ዘንድ መስቀል ይከበር ነበር።

**ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት መጣ?**

የጌታ መስቀል ለብዙ ዓመታት በእየሩሳሌም ከቆየ በኋላ ነገሥታት መስቀሉን ለመውሰድ ጠብ ፈጠሩ። በዚህ ጊዜ የአንጾኪያ፣ የኤፌሶን፣ የአርማንያ፣ የግሪክ፣ነየእስክንድርያ፣ የመሳሰሉት የኃይማኖት መሪዎች ጠቡን አበረዱት። ከዚያም አያይዘው በእየሩሳሌም የሚገኘውን የክርስቶስን መስቀል ለዐራት ከፍለው በስምምነት ተካፍለው ከሌሎች ታሪካዊ ንዋያተ ቅድሳት ጋር በየሀገራቸው ወስደው በክብር አስቀመጡት። የቀኝ ክንፉ የደረሰው ለአፍሪቃ ስለነበር ከታሪካዊ ንዋየ ቅድሳት ጋር በግብፅ የሚገኘው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ተረክቦ ወስዶ በክብር አስቀመጠው፡፡

ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዳግማዊ ዳዊት የግብፅ ክርስቲያኖች በአማሌቃውያን ከሚደርስባቸው ተጽዕኖ ነጻ እንዲወጡ በማድረጋቸው የግብፅ ፓትርያርክ የከበሩ ስጦታዎችን ላኩላቸው። ንጉሥ ዳግማዊ ዳዊት ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው ወርቅ ሳይሆን ጌታ የተሰቀለበትን መስቀሉን እንደሆነ ገለጹላቸው። በመሆኑም የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግማደ መስቀሉን ከሌሎች ንዋየ ቅድሳት ጋር ለኢትዮጵያ ሰጥታለች። ይህ ግማደ መስቀል በግሸን ማርያም ገዳም በእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ኢትዮጵያን እየባረከ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መስቀልን ከሐዋርያት በተማረችው መሠረት የወርና የዓመት በዓል ሥርታ ታከብረዋለች። መስከረም 16 ቀን ደመራ ደምራ ጸሎትና ምሥጋና ታቀርባለች። ቅዱስ መስቀል ከተቀበረበት መሬት በእሌኒ አማካኝነት መገኘቱን ስታስብ በአሁኑ ዘመን ከብዙ ሰዎች ልቡና የተሠወረው መስቀል እንዲገለጥላቸው ትጸልያለች።

በመስቀል የሚገኘውን በረከት እየተቀበለች በመስቀል የሚመሰለውን መከራ ሁሉ ትታገሣለች። መስቀል በካህናት በምእመናንና በምእመናት ልቡና ተስሏል። በአንገታቸውና ልብሳቸውም መስቀል አለ። ሥራ ሲጀመርና ምግብ ሲቀርብ በመስቀል አምሳያ ይማተባል። መስቀል ለሁሉም ነገር መጀመሪያና መጨረሻ ነው። "እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" (ማቴ 16፡ 24) እንዳለ ጌታችን ቤተ ክርስቲያናችን ዕለት ዕለት መስቀሉን ትሸከማለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ መስከረም 16 ቀን የምትደምረው ደመራ አገራዊ አንደምታም አለው። የመስቀል ደመራ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፡ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እውቅና ተሰጥቶት ዓለም አቀፋዊ ቅርስ ተብሎ ተመዝግቧል።

«የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚብሔር ኃይል ነው» (1ቆሮ 1፥18) በሚል መጽሀፍ ቅዱሳዊ አስተምሮ የኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታዮች በዓሉን በድምቀት ያከብሩታል። በደመራ ደምረው ችቦ ለኩሰው የሆያ ሆየ ጭፈራ በዜማ በመጨፈር ይጫወታሉ። ይህ የመስቀል ደመራ በዓል በዩኔስኮ የተመዘገበ በመሆኑ ከእምነቱ ተከታዮች በሸገር የሀገር የቱሪስት መስብ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያከብረውና ሊንከባከበው ይገባል እንላለን!።

**ንግሥት እሌኒ ልጇ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነላት ወደ እየሩሳሌም ሔዳ መስቀሉን ለመፈለግ እንዲሁም በእየሩሳሌም ያሉ ቅዱሳት መካናትንና አብያተ ክርስቲያናትን ለማሳነፅ ለእግዚአብሔር ተሳለች**

# ስፖርት



# የወጣት ብሔራዊ ቡድኑ ለሴካፋ ዋንጫ ዝግጅቱን አጠናክሮ ቀጥሏል

**ብርሃን ፈይሳ**

የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ (ሴካፋ) የወንዶች ከ20 ዓመት በታች ዋንጫ ከመጪው ሳምንት መጨረሻ ጀምሮ በታንዛኒያ ዳሬሰላም ከተማ አዘጋጅነት ይካሄዳል። ይህ ውድድር በቀጣዩ የፈረንጆቹ ዓመት ለሚካሄደው ከ20 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ዞኑን ወክለው የሚካፈሉ ሁለት ሀገራትን ለመለየት እንደ ማጣሪያ የሚያገለግልም ነው። የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድንም ለሴካፋ ዞን ከ20 ዓመት በታች አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ውድድር ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል።

በውድድሩ ተሳታፊነታቸውን ያረጋገጡት የዘጠኝ ሀገራት ብሔራዊ ቡድኖች በሁለት ተከፍለው የሚፎካከሩ ይሆናል። በመጀመሪያው ምድብ አዘጋጇ ታንዛኒያ ከሱዳን፣ ርዋንዳ፣ ጅቡቲ እና ኬንያ ጋር የተደለደሉ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በምትገኝበት ቀጣዩ ምድብ ደግሞ ቻምፒዮና ዩጋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን እና ብሩንዲ ይገኛሉ። ለሁለት ሳምንታት ያህል የሚደረገው ውድድር መስከረም 26 ጥቅምት 10/2017 ዓ/ም የሚቆይም ይሆናል፡፡

በዚህ ውድድር የሚካፈለውን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ለማዘጋጀትም በዋና አሠልጣኝነት ስዩም ከበደ፣ በረዳት አሠልጣኝነት ደግሞ ዐቢይ ካሳሁን እንዲሁም አምሳሉ እስመለዓለም በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከቀናት በፊት መሾማቸው ይታወቃል። ጥሪ የተደረገላቸው ተጫዋቾችም ከመስከረም 07/2017 ዓ/ም አንስቶ በመሰባሰብ ወደ ዝግጅት ገብተዋል። መቀመጫውን ካሌብ ሆቴል ያደረገው የኢትዮጵያ ወጣት ቡድን በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ዝግጅቱን አጠናክሮ በማከናወን ላይም ይገኛል።

ባለፉት የዝግጅት ቀናት ጥሪ ተደርጎላቸው ከቡድኑ ጋር ሲሠሩ የቆዩ አራት ተጫዋቾች እንዲሁም ሶስት ግብ ጠባቂዎች የተቀነሱ ሲሆን፤ በምትካቸው ሌሎች አራት ተጫዋቾች ማለትም አለልኝ ሙሉነህ እና ዳዊት ካሳው ከስሪ ፖይንት አካዳሚ፣ መድህን ተክሉ ከወልቂጤ ከተማ እንዲሁም ይበልጣል ኤልያስ ከስፔኑ ቢ ዋን አካዳሚ ስብስቡን ተቀላቅለው ልምምዳቸውን እያከናወኑ መሆናቸውም ታውቋል። በመጀመሪያው ጥሪ ላይ ያልተገኙት የድሬዳዋ ከተማ እና ቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ ተጫዋቾችም ወደ ዝግጅት ገብተዋል። በዚህም መሠረት የመጨረሻው የቡድኑ ስብስብ በመጪው እሁድ መስከረም 19/2017 ዓ/ም የሚታወቅ መሆኑን ፌዴሬሽኑ ጠቁማል።

ዋና አሠልጣኝ ስዩም ከበደ በሥራቸው ካሉ ወጣት አሠልጣኞች ጋር በመሆን ለተጫዋቾች የመጀመሪያ ጥሪ ማድረጋቸውን በማስታወስ፣ ተጫዋቾቹም ከ20 ዓመት በታች ሊግ እንዲሁም ባላቸው ብቃት በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የመጫወት ዕድል ያገኙ ወጣቶች ሲሆኑ፤ ኢትዮጵያን ለመወከል ይመጥናል የሚባል ቡድን ለመመስረት ተሰባስበዋል። በመጀመሪያው ጥሪም ከ40ዎቹ 33 የሚሆኑት ተገኝተዋል። ባለው አጭር የዝግጅት ጊዜም ጠንካራ ቡድን ይዞ ውድድሩ ላይ ለመቅረብ እንዲሁም ዋናውን ብሄራዊ ቡድን ሊረከቡ የሚችሉ ወጣቶች በመሆናቸው ይህንን ያማከለ ዝግጅት በመደረግ ላይ እንደሚገኝም አብራርተዋል።



**የወጣት ብሔራዊ ቡድኑ በአበበ ቢቂላ ስቴድየም ልምምዱን ቀጥሏል፣**

ውድድሩ እአአ ከ1971 አንስቶ በመካሄድ 53 ዓመታትን ያስቆጥር እንጂ በወጥነት ከመካሄድ ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት እየተደረገ አሁን ካለበት ደርሷል። በዚህ ውድድር ዩጋንዳ ለ5 ጊዜያት ዋንጫውን በማንሳት ስኬታማ ሀገር ስትሆን ከሁለት ዓመት በፊትም አሸናፊ መሆኗ የሚታወስ ነው። ኢትዮጵያ በበኩሏ እአአ በ1995፣ 1996 እና 2005 ለሶስት ጊዜያት ቻምፒዮን ለመሆን ችላለች።

## ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የገጠር መንገድ ትስስር ለምግብ ዋስትና

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ኢትዮጵያ በ2030 የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት ለመሆን በምታደርገው የልማት ጉዞ የመንገድ ዘርፉ ማደግ ሁነኛ አጋዥ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ይህ ዘርፍ በሀገሪቱ የሚከናወኑ ምጣኔ ሀብት እና ማኅበራዊ እድገት ጉልህ ድርሻ ያለው መሆኑ እሙን ነው። ይህን በመረዳት የፌዴራል መንግሥት ባለፉት የልማት ዕቅዶቹ ትኩረት ከሰጣቸው ዓበይት ዘርፎች አንዱ የመንገድ ዘርፍ ነበር። በዚህም ዘርፉ የምጣኔ ሀብቱን ዕድገት በማስቀጠል ብሎም ይበልጥ ተተኪ የሌለውን የደጋፊነት ሚናውን በላቀ ሁኔታ እንዲወጣ የሚያስችሉ እ.አ.አ ከ1997 ጀምሮ ትልልቅ ግቦችን በመያዝ ለተግባራዊነታቸው ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል።

መንግሥት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የምጣኔ ሀብት እና ማኅበራዊ ዕድገት ዘላቂነት እና ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለውን የተደራሽነት እና የእንቅስቃሴ ፍላጎትን (Accessibility and Mobility Demand) ከወዲሁ ታሳቢ ያደረገ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ፣ ጥገና እና እንክብካቤ ሥራን ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚካሄድበት የልማት ማዕቀፍ ዘርግቶ እያካሄደ ይገኛል፡፡

የኢፌዴሪ ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በያዝነው በጀት ዓመት መባቻ ለቀጣይ አምስት ዓመታት ለመንገድ መሠረተ-ልማት የሚውል 300 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ድጋፍ ይፋ ያደረገውም ከላይ የጠቀስነው ልማት ለማሳለጥ ነው። ይህም የገጠር መንገድ ትስስር ለምግብ ዋስትና ድጋፍ ፕሮግራምን (RURAL CONNECTIVITY FOR FOOD SECURITY PROGRAM) ለመተግበር የሚያስችል ነው። ድጋፉ የገጠር መንገዶችን ከቀበሌ እስከ ዋና መንገዶች ጋር በማስተሳሰር በገጠር የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሠጠው መርሃ ግብር እንደሆነ ሚኒስትሯ ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ አብራርተዋል፡፡

ፕሮግራሙ በፍትሐዊ መንገድ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀመር መሠረት በ12 ክልሎችና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚተገበር ነው። በአጠቃላይ በሀገሪቱ በ126 ወረዳዎች ከፍተኛ የግብርና ምርት በሚመረትባቸውና ቆላማ አካባቢዎች የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራው እንደሚከናወን ሚኒስትሯ አስታውቀዋል።

መርሃ ግብሩን በይፋ ለማስጀመር የክልል ከተሞች አመራሮችና ባለሙያዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ፕሮጀክቱን ለመተግበር ባለፈው ጳጉሜን 2 ቀን 2016 ዓ.ም ሱልልታ ከተማ የአፍሪካ አመራር አካዳሚ የምክክር መድረክ ተካሂዶ ነበር፡፡

ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ በዓለም ባንክና የኢፌዴሪ መንግሥት ባደረጉት ስምምነት መሠረት 300 ሚሊዮን ዶላር ከዓለም ባንክ ሙሉ በሙሉ ርዳታ እና 107 ሚሊዮን ዶላር ደግሞ ከክልሎች በጀት እንደተገኘ ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ ተናግረዋል። ለፕሮጀክቱ በድምሩ 407 ሚሊዮን ዶላር ፈንድ ተፈቅዶ ከ2017 በጀት ዓመት ጀምሮ ለአምስት ዓመታት በሁሉም ክልሎች እና በድሬዳዋ የከተማ አስተዳደር ተግባራዊ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

የገጠር መንገድን ተደራሽነት ለማሳደግ ከ 7 ሺህ 500 በላይ ኪ.ሜ አዲስ የወረዳ መንገድ ግንባታ ወይም ደረጃ ማሻሻል ሲሆን 10 ሺህ 71 ኪሎ ሜትር ደግሞ የመንገድ ጥገና እንደሚደረግ ሚኒስትሯ አስታውቀዋል። ከ10 ሺህ በላይ የቆላማ አካባቢ መሻገሪያ ድልድዮች እንደሚሠሩና ከአዳዲስ የመንገድ ግንባታ በተጨማሪ፤ ከዚህ ቀደም በተለያዩ የሀገሪቱ ከፍሎች ተጀምረው ያልተጠናቀቁ መንገዶችን የማጠናቀቅ ሥራ እንደሚከናወን ታውቋል፡፡

ይህ አዲሱ የገጠር መንገድ ትስስር ለምግብ ዋስትና ድጋፍ ፕሮግራም (RURAL CONNECTIVITY FOR FOOD SECURITY PROGRAM) የገጠሩን ማኅበረሰብ ትስስርና ለተለያዩ መሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽ ከማድረግ ባለፈ በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ባለቤትነት ከዚህ ቀደም ሲከናወኑ የነበሩ የገጠር መንገድ ሥራ ንዑስ ፕሮግራሞችን በማቀናጀት እና ወደ አንድ ሀገራዊና ወጥ ወደሆነ የአሠራር ሥርዓት እና ደረጃ እንዲመጡ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

ይህም ውስን የሆነውን የሀገር ሀብት ብክነትን በሚቀንስና በተቀናጀ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል አሠራርና አደረጃጀት ለመፍጠር ያስችላል። ከዚህ ባለፈ ይህ ፕሮግራም ሲቀረፅ ቀደም ሲል የነበረውን ፕሮግራም ትግበራ በመገምገም እና ለቀጣይ አስር ዓመታት የተቀመጠውን ሀገራዊ ርዕይ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ በቀበሌ ደረጃ ያሉ መንደሮችን እና በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉ ማኅበረሰቦችንም ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ተሞክሮዎችን ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅቷል።

የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወንድሙ ሴታ (ኢ/ር) በበኩላቸው ፕሮግራሙ ለአምስት ዓመታት የሚቆይና በርካታ የሀገር ውስጥ መካከለኛ የኮንስትራክሽን ተቋራጮች የሚሳተፉበትና ሰፊ የሥራ እድል እንደሚፈጥር ጠቁመዋል። መንገዶቹ ሲገነቡ ለትውልድ የሚተላለፉና የገጠሩን ኅብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ በእጅጉ እንደሚቀይረውና የግብርና እምቅ አካባቢዎችን ከገበያ ጋር እንደሚያገናኙም አስረድተዋል።

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ የገጠሩን ማህበረሰብ እርስ በርስ እና ከማእከላት ጋር በማስተሳሰር እና ተነጥለው ያሉ አካባቢዎችን በማገናኘት እና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ የገጠሩን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል እና ለምግብ ገበያ እና ለተለያዩ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ማሳደግ ነው።

ይህንን ለማሳካትም የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን አቅራቢያቸው ከሚገኝ ዋና መንገድ ጋር ማገናኘት፣ እምቅ አቅም የግብርና ምርት ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ፋይዳ ያላቸውን መንደሮች እና መዳረሻዎች ማገናኘት፣ በመልከአ ምድራዊ አቀማመጣቸው ምክንያት ተነጥለው ያሉ የገጠር አካባቢዎችን ተደራሽ ማድረግ እና ቆላማ አካባቢዎች ያሉ የመሻገሪያ ችግሮችን መፍታት በፕሮጀክቱ እንደ ዓላማና ግብ የተያዙ ናቸው።

የተቀመጡትን ዓላማዎች ለማሳካት በትኩረት መሠራት ያለባቸው ጉዳዮች ተለይተዋል። ከነዚህም መካከል ተጀምረው ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ቅድሚያ ሰጥቶ ማጠናቀቅ (ስትራክቸሮችን ጨምሮ)፣ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ፕሮግራሞች የተገነቡ መንገዶችን መንከባከብ እና መጠገን፣ የክልሎችን የገጠር መንገድ የጥገና አቅም መገንባት፣ ከፍተኛ የግብርና ምርት ያለባቸውን ያልተገናኙ ቀበሌዎችን ማገናኘት፣ ጥራት ላለው የሥራ እድል ፈጠራ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ የግብርና የግብይት ዲጂታል ሥርዓት መገንባት፣ አካባቢያዊ እና የሀገር ውስጥ ሀብት አቅምን ጨምሮ ማጎልበትና በስፋት መጠቀም እንዲሁም የአስፈጻሚ ተቋማትን እና ፈጻሚ አካላትን አቅም መገንባት መሆናቸውን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡